# ፊታውራሪ በላይ።
# ታሪክ በምሳሌ፤

## ከራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣

**ባ፲፱፻፵፪ ዓመተ ምሕረት በዋሺንግቶን ተጻፈ።**

፩ኛ አዲስ አበባ ፲፱፻፵፰ ዓመተ ምሕረት፤
፪ኛ አዲስ አበባ ፲፱፻፶፯ ዓመተ ምሕረት፤
፫ኛ አዲስ አበባ ፲፱፻፷፯ ዓመተ ምሕረት፤

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ፊታውራሪ በላይ።

# ታሪክ በምሳሌ፤

ከራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣

ባ፲፱፻፵፪ ዓመተ ምሕረት በዋሺንግቶን ተጻፈ።

አሜሪካ U.S.A

፩ኛ አዲስ አበባ ፲፱፻፵፰ ዓመተ ምሕረት፤

፪ኛ አዲስ አበባ ፲፱፻፶፮ ዓመተ ምሕረት፤

፫ኛ አዲስ አበባ ፲፱፻፷፯ ዓመተ ምሕረት፤

# በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ።

ፊታውራሪ በላይ

ጌታው አልዩ

ወይዘሮ ተዋበች

ነጋድራስ ገብረ መድኅን፣

አለቃ ሥዩም

ባሻ ካሣሁን፣

ሻለቃ ጌታነህ፣

ዳኞች፣

ጐረደማኞች ናቸው።

# መቅድም።

በዚህች ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው የፊታውራሪ በላይንና የቤተ ሰቦቹን የሕይወት ታሪክ፤ የቀድሞውን በኢትዮጵያ ክፍል አገሮች ውስጥ የነበረውን አስተዳደር፤ ያገሩን ባላባቶች ሥልጣን (የፌዋደል) አገዛዝ።

ጠንቋዮች፤ የሚመልስን ነገር አስቀድመው እያሰቡና እያረጋገጡ በማመልከት፤ የሚያደርጉትን ያታላይነት አሠራር፤ በሃይማኖት ልዩነት የነበረውንም ነገር።

ሰው ባገኝና በተመቸው ጊዜ በቃኝ ሳይል በንፍገት ሐሳቡና ምኞቱ መልካም መሬትንና ሌላም ደኅና የሆነ ነገርን ሲያይ ሰበብ ፈልጎ ነቅሎ መሬቱንም ሆነ ሌላም የሚሻውን የራሱ ለማድረግና የግፍ ሥራ ለመሥራት መጣጣሩን የሚገልጽ ነው።

የግፍንም ሥራ ሠሪ ሁሉ ቢቈይም እንኳ ብድሩን መከፈሉ የማይቀር መሆኑን እያሳየ፤ ጥቂት ርኅራኄና ደግነት ያላቸውንም በመከራ ከተመከሩ በኋላ የእግዚአብሔር ረድኤት ከሁሉም አድኖ እንደ ገና በደስታ አድሶ ከተበታተኑበት ሁሉንም ሰብስቦ ማገናኘቱን እያመለከተ፣ በቅንነት መልካም ሥራ የሚሠራ ሰውም ሁል ጊዜ ከሁሉ የሚበልጠው ተግባር መፈጸሙን የሚያስረዳ ነው።

ይህችውም መጽሐፍ በቀጥታው የምታሳየው፤ የፊታውራሪ በላይን የሕይወት ታሪክ ሲሆን፤ ደግሞ ስሜቱ የኢትዮጵያን በኢጣሊያ ፋሺስት አወዳደቅና አነሣሥ የሚያሳይ ነው።

አንባቢዎችን ደስ እንደሚያሰኝ እመኛለሁ።

**ራስ እምሩ ኃ. ሥ.**

# ምዕራፍ ፩።

በጐጃም አውራጃ ግዛት ውስጥ አነደድ በሚባል በትንሽነቱ ያገራችንን ትምህርት እየተማረ አድጎ ጥቂት ከፍ እንዳለ ለጐጃም ባላባት ለደጃች ተድላ ጓሉ አሽከርነት አድሮ ሳለ ባጼ ቴዎድሮስ ዘመን ከጌታው ጋራ ጐንደር ድረስ አብሮ ሄዶ እያገለገለና እየተላላከ አልተለያቸውም ነበር።

ያጼ ቴዎድሮስ የመንግሥታቸው አገዛዝ እየተበላሸና እየደከመ ሲሄድ ደጃች ተድላም የጐጃም ዋና ባላባት እንደ ሌሎቹ አገሮች ባላባቶች ሁሉ ጐንደር ከተማ የተቀመጡት ግዞተኛ ሆነው ነበርና ካጼ ቴዎድሮስ ከድተው ጠፍተው ወዳገራቸው ጐጃም ሄዱ። ያገራቸውም ሕዝብ ተቀብሎ አብሮ ሁኖ ስለ ረዳቸው በጐጃም ውስጥ ያሉትን አጼ ቴዎድሮስ የሾሟቸውን ሹሞች እሺ ያለውን በውድ እንቢ ያለውንም ሁሉ በግድ እየተዋጉ ድል እያደረጉ እየሻሩ መላውን ጐጃምን ይዘው አገሩን ገዥ በነበሩበት ወራት ሁሉ ያ ወጣት በላይ ካሣ አሽከራቸው በሚቻለው ዐቅሙ ጌታውን እያገለገለና እየረዳ አልተለአይቸውም ነበርና የጐጃምን ግዛት ደጃች ተድላ አረጋግጠው እንደ ያዙ በዚያን ዘመን የነበሩት ያገሩ መሳፍንቶች (ባለሥልጣኖች) እንደሚያደርጉት አሰጣጥ ሁሉ ለአገልጋይ አሽከራቸው ለወጣቱ በላይ ካሣ ስለ አገልግሎቱ ባነደድ ወረዳ ውስጥ በተወለደበት አገር በርስቱ ዙርያ ያሉትን ዐሥራ አምስት ገባሮች ጨምረው ለዚሁ አሽከራቸው ርስተ ጒልት እንዲሆንለት መዝገብ አስገብተውና አሳውጀው «ማለት ዐዋጅ አስነግረው» ሰጡት። ይኸውም የሆነው ገባሮቹ የሚገብሩት ግብር ሁሉ ወደሳቸው የሚገባው ሁሉ እየሆነ ከነመሬታቸው ለሱው ርስት ሆነው ለልጁ፤ ለልጅ ልጁ እንዲተላለፍ አድርገው ነበር። የሱም የወራሾችም ግብር ዘመቻ በሆነ ጊዜ ሥንቅን ራሱ አሰናድቶ አብሮ ከጌታው ጋራ እንዲዘምት ብቻ የተደረገ ግብር አድርገው ነው የሰጡት።

ይኸንኑም የሰጡትን ርስት ጒልት ወደ ወረዳው ሹማምንቶች ትእዛዙ ተላልፎለትና ተረክቦ ዐዋጁን አስነግሮ ይዞ ተቀመጠ። ከዚሁም ከተሰጠው መሬት ውስጥ የነበሩት ገባሮች ብዙዎቹ ዘመዶቹ ስለ ነበሩ፤ እርሱ

በማግኘቱ ከየግብራቸው የሚሻሻልላቸው ስለ መሰላቸው የሱ ማግኘት ደስ አሰኝቷቸው ነበር።

አንዳንዶቹ ገባሮች ግን ዝምድና አልነበራቸውምና ለርሱ ገባር መሆንን የማይወዱም ቢሆን፤ ያገሩ መስፍን ዋናው ባለሥልጣን ያደረገውን ነገር ለመቃወም ስለ አልቻሉና ስለማይችሉም ዝም ብለው ላቶ በላይ ካሣ እየታዘዙና እየተገዙ ግብራቸውን በውድም ሆነ በግድ እየገበሩለት ተቀመጡ። ስለ ሆነም እነዚህ ባዕዶች የሆኑት ገባሮች በሥራም ሆነ በየሌላውም በማናቸውም ነገር ሁሉ ዘምድ እንደ ሆኑት ገባሮች ስለማይራራላቸውና ከግብራቸውም የሚቀልላቸው ስለ ሌለ ያቀማመጣቸው ኑሮ በብስጭት ሆነ።

የሚያበሳጫቸውም በቀጥታው ለደጃች ተድላ ቢገብሩ ግብሩና ሥራውም ባይቀርላቸው ያቶ በላይ ዘምዶች ባልንጀሮቻቸው ገባሮች በዝምድናቸው ምክንያት አንዳንድ ነገር ከተለመደው ግብራቸው አቅልሎላቸው አሻሽሎላቸው እነሱን ሙሉውን ግብር ስለሚያስገብራቸውና በሥራም ረገድ ያለ ምሕረት ስለሚያሠራቸው ትልቅ ያድልዎ ነገር ዘወትር በማየታቸው ነበር።

ከነዚህም ባዕዶች ከሆኑት ገባሮች ውስጥ በጣም አብዝቶ የሚቈረቈርና የሚበሳጭ ቢረሳው የሚባለው አንድ ገባር ስለ ነበረ፤ ባለርስተ ጕልቱ አቶ በላይ አሳቡን በሁኔታው ሁሉ ተመልክቶና ዐውቆበት እየጠላው በያንዳንድ ምክንያት ሁሉ የመጫን ሥራ በተለይ በሱ ላይ ይሠራበት ነበር። ይልቁንም በዚሁ ነገር ቢረሳው በመበሳጨት እየተመረረ የካሣ ልጅ መጥቶ በላያችን ላይ የተሾመው ለጌታ አድሮ በማገልገሉ ብቻ አይደለምን እኔም ላንድ ጌታ አድሬ ባገለገል እንደዚሁ ያለ ትዳር አላጣም ይሆናል እያለ በሕልሙም ሆነ በውኑም የሚያስበው ይኸንኑ ነበር።

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በልቡ ነገሩን ሲያወጣ ሲያወርድ ቤቴን፣ ትዳሬን ትቼ ሄጄ ደግሞ ላልሆነ ጌታ አድሬ እሱም ሳያልፍለት እኔንም ጭምሮ ይጠፋ ይሆን? የማለት ጥርጣሬ ስለ ወደቀበት እንደ ምንም ብዬ ችዬ እየገበርኩ ከዚሁ ካባቴ መሬት ብቈይ ይሻላል ብሎ ተቀምጦ ሳለ፤

ባለርስቱ አቶ በላይ ካሣ ከገባሮች ዘመዶቹ አንዱን ግብሩን ትቶ (መልምሎ) ሾሞ ነበርና ይኸውም የተሾመው ገባር ቢረሳውም የማይወድ በመሆኑ በብዙ የሰበብ ምክንያት እየፈለገ ስላጠቃው ካቶ በላይ ካሣ ላይ እየከሰሰ ጥቃቱንና ጉዳቱን ቢናገር የሚያገኘው ብይንና ፍርድ ምንም የሚጠቅም አልሆን አለው። ምክንያቱም የዚሁ የቢረሳው የገባርነቱ መሬት ውሃ የሚገባው ላታክልት የሚሆን ደኅና መሬት ነበርና ተመርሮና መሬቱንም ለቆ ቢሄድለት አቶ በላይ ይፈቅድ ነበርና ነው።

ይኸውም ቢረሳው የሚባለው ገባር ከቀን ወደ ቀን ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥቃትና የግፍ መጉላላት እየበዛበት በመሄዱ ወደ በላይ ዳኝኖች አቤት ለማለት ብሄድም ባልጉልት አቶ በላይ የጌቶቹ ባለሙዋልና በግቢውም የታወቀ ባለብዙ ወገን በመሆኑ መጉላላት ነው የሚተርፈኝ በማለት ተስፋ አልነበረውም። ስለዚህ ፊት አስቦት በነበረው ነገር ላይ እንደ ገና ተመልሶ ለጌታ አድሬ ይኸን ገባርነቴን ትቼ ሄጄ የዕድሌን ብፈልግ ይሻላል። እነዚህ ሰዎች ምንም በመሬቴ የሚያስቀምጡኝ አይደሉም እያለ ባሳቡ ለመሄድ እየወሰነ ወዲያው ደግሞ ትልቅ ጥርጥር እየገባበት ምድሬንም ትቼ ሄጄ ከዚህ የከፋ ነገር ያገኘኝ እንደ ሆነ እንዴት እሆናለሁ የቆጥ አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች የሚሉት ተረት እንዳይደርስብኝ እስቲ ደግሞ ሁሉንም ታግሼ ልቈይ ብሎ በሚችለው መጠን የታዘዘውን እየሠራ ተቀምጦ ነበር።

አቶ በላይም የሾመው ሹም ገባር ቢረሳውን በርሻ ወራት ወደ ሩቅ ቦታ በመላክ ሥራውን እያሰናከለ የሚገብረውን እኸልና ማር በስፍር እየተጫነ አልሞላልህም በማለት እያስጨመረ ጥቂት አሞት እንኳ ከሥራ ቢቀር የጻፊን ገንዘብ እያስከፈለ ይኸን በመሰለው ሁሉ አብዝቶ ያስቸግርወ ነበር። ባለርስቱ አቶ በላይም ገባሩን ቢራሳውን ንም ቢጠላው በግፍ የመበደሉ አኳኋን ሰውነቱን እየተሰማው ከልቡ እንኳ ባይሆን በሰው ፊት መልካም ሰው መስሎ መታየትን የሚወድ ነበርና ይኸንን ሰው አታጉላሉት እያለ አንዳንድ ጊዜ ለቤተ ሰቦቹ ይነግር ነበር። ነገር ግን ቤተ ሰቦቹና ሹሙ ይልቁንም የግፍ ሥራ እያበዙበት በመሄዳቸው፤ ባለርስቱም ምንም ሊያድነው ባለመቻሉ ቢረሳው በፍጹም ተመርሮና ተበሳጭጦ መሪቱን ቤቱን፤ ትዳሩን ትቶ ለመሄድና ለጌታ ለማደር ቍርጥ አሳብ አደረገ።

ይኸውም ሲሆን የሚያድርለት፤ ወደፊትም ዕድል ያለው ጌታ ማን እንደ ሆነ ለማወቅ በጣም ስለ አሰበበትና አስቀድሞም፣ ለማረጋገጥ ስለ ፈለገ፤ ከመንጋዎቹ መካከል አንዱን ደኅና በግ መርጦ ሁለት ያሞሌ ጨው ጨምሮ ይዞ ካንድ ጠንቋይ ደብተራ ዘንድ ለመጠየቅ ሄደ።

የሄደበትም መሪጌታ መአልኩ የሚባል የዚያው ያገሩ ያነደድ ተወላጅ የታወቀ ጠንቋይ ደብተራ ነበር። ይኸውም መሪጌታ መልአኩ አገሩ አነደድም ቢሆን ብዙ ጊዜ ወደ ከተማ እየሄደ በከተማው ዋና ደብር በደብተርነት ተተክሎ መሪጌታ ተብሎ እያገለገለ ደግሞም በዚያው ላይ በምድረ ግቢው የጽሕፈት ሥራ መሳይ እየሠራ የሠለጠነ ስለ ሆነ፤ ብዙ ወሬ የሚሰማውና የብዙም ነገር አኳኋን መላ ጭምር ለይቶ የሚያውቅ ብልኅ ሰው፣ ነበር።

ይኸውም ጮሌ ጠንቋይ በዚሁ በጥንቈላ ሥራው ብዙ ሰላሚጠቀምበት እየመጡ የወደፊቱን ነገር ለማወቅ ለሚያስጠነቍሉት ሁሉ አላውቅም ለሚያስጠነቍሉት ሁሉ አላውቅም የሚላቸው ምንም ነገር አልነበረውም። ጒዳያቸውን እየጠየቀ ገንዘብ እየተቀበለ መጽሐፉን እየገላለጠ ለጠየቁት ነገር የሚመስለውን እየፈለሰፈና እያሰበ ይኸ ይኸ እንደዚህ ይሆናል እያለ በድፍረት ጭምር የሚናገር ነበር። በጥንቈላውም ይሆናል ከሚለው ካሥር አራቱ ያህል ጊዜው አጋጥሞት እየሆነለት አመስጋኙ ብዙ ስለ ሆነ፤ እሱን የመሰለ ጠንቋዩ የለም። የተናገረው ሁሉ ይሆናል እያሉ ያገሩ ሰዎች የሚያደንቁት አታላይ ነበር። ካሥሩ ስድስቱ ይሆናል ብሎ ሳይሆን ቢቀርም የሚያስብበትና የሚዘከርበት ሰው አልነበረም። በዚያን ጊዜም ደብተራ መልአኩ የተቀመጠው አነደድ ከሚባለው አገር ነበርና አቶ ቢረሳው ሄዶ ሁለት ጨውና በጉን ከሰጠ በኋላ የመጣበት ጒዳይ ለጌታ ማደር መሆኑን የሚያድርለትም ጌታ ዕድል ያለው እያደር የሚያድግ ማን እንደ ሆነ ከዚያውም ጌታ ጋራ የሱ ዕድል የተስማማ የተባበረ መሆኑን አለመሆኑን አረጋግጦ ለይቶ እንዲያመለክተው እየለመነ አስታወቀው። ይህንኑም ለዚህ ሞኝ የዋህ ገባር ያን ጊዜውን መልሱን ለመንገር መሪጌታ መልአኩን እጅግ የሚያስቸግረው አልነበረም። ነገር ግን ከዋጋው ጥቂት ለማስጨመር ስለ ፈለገ የጠየቅኸኝ

ጉዳይ ምንም በጣም አዋኪም ባይሆን ጥቂት ቀን ውለህ አድረህ ብትመለስ መልካም ነው፤ ዛሬ ሌላ ብዙ ሥራ አለብኝ ብሎ ያስታወቀውን ነገር በማስታወሻአው ጽፎ ያመጣለን ተቀብሎ አሰናብቶት ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ገባር ቢረሳውም እጅግ ያሰበበት ነገር ስለ ሆነ ደብተራው የገንዘብ ጭማሪ መፈለጉ ስለ ታወቀው ከሦስት ቀን በኋላ ደግሞ አንድ በግ ይዞ ሄዶ ሰጥቶ ያንኑ ነገሩን እንዲያስታውቀው አበርትቶ ለመነው።

በዚያም ወራት ደጃች ተድላ ሞተው ጐጃምን የሚገዙ ደጃች ጐሹ የሚባሉት ያገሩ የጐጃም ባላባት ነበሩ። ያን ጊዜም ደጃች ተሰማ የሚባሉት ባላባት ልጅ ባላምባራስ አዳል ይገዛሉ እየተባለ በየባሕታዊውና በግቢ ደምቆ ይወራ ነበርና መሪ ጌታ መልአኩም ይህን ደኅና አድርጎ ስለሚያውቅ ላቶ ቢረሳው ሂደህ ለባላምባራስ አዳል እደር ዕድልህ ከሱ ጋራ ነው፣ እሱም የሚያድግ ዕድላም ጌታ ነው። እንደዚህም ስላልኩህ በገዛ እጅህ ዕድልህን ደግሞ እንዳታጠፋው ትዕግሥተኛና ቻይ ሆነህ የሚይዙህን ሁሉ በቅንነት እየፈጸምህ ከሹማምንቶችም ተስማምተህ አገልግሎትህን ማሳመር ነው፤ ከዚያ ነውና ዕድልህ በሁሉም ነገር ሳይቀናህ አይቀርም ብሎ ስለ አስታወቀው፤ ገባር ቢረሳው ደስ ብሎት አንዲት ብር በመቀነቱ ቋጥሮ የያዛት ነበረችውና ስለ ደስታው ያችንም አውጥጦ ሰጥቶት ወደ ቤቱ ሄደ።

ከጥቂት ሳምንቶችም በኋላ ቢረሳው ከብቶቹን ሽጦ ርስቱን ትዳሩን ቤቱን ንብረቱን ሁሉ ትቶ ባላምባራስ አዳል ወደ አሉበት አገር ሂዶ አልጋፋሪያቸው አሽከር ሆኜ ለማደር ሎሌ ሁኜ ለማገልገል መጥቻለሁ ብሎ ስለ አስታወቀው፣ አጋፋሪውም ለባላምባራስ አዳል አመልክቶ ወዲያውም አገናኝቶት ባልደረባውን ተቀብሎ የወታደርነት አገልግሎቱን ጀመረ። የጐጃምም ባላገር የወታደርነትን ኑሮ ለመልመድ እጅግ አስቸጋሪው አይደለምና ሲወጡ እየወጣ በየተላከበትም መልእክቱን በደኅና እየፈጸመ ታውቆ በደኅና ተቀመጠ። ቢረሳውም መሪጌታ መልአኩ የነገረውንና የመከረውን ሁሉ እያስታወሰ ምንም የሚያበሳጭና የሚያስቸግርም አንዳንድ ነገር ቢያገኘው ሁሉንም በታላቅ ትዕግሥት ችሎ የሚያሳልፈው ብዙ ነገር ነበረው።

ያ ባለርስት ጉልት አቶ በላይም ጌታው ስለ ሞቱበት በጣም አዝኖ ቈይቶ ደጃች ጐሹም ያውቁት ነበርና መታያውን አሰናድቶ ይዞ ሂዶ ስለ ተገናኘ፤ ርስቱን አጽድቀውለት ከዚያም በኋላ ሚስት አግብቶ ልጆቹ ወልዶ ባገር የታወቀ ጨዋ ቤተ ክርስቲያን አዘውትሮ ሳሚ ሆኖ ደስ ብሎት ሲኖር ከጥቂት ወራቶች በኋላ ደጃች ጐሹም ሞቱና በእሳቸው እግር ደጃዝማች ተሰማ ገብተው እሳቸውም ስለ ሞቱ፤ ነገሩ ሁሉ ተለዋውጦ ደጃች አዳል ልጃቸው ጐጃምን በመላው ዋና ሆነው ስለ ያዙ፤ ያ ቢረሳው የሚባለው አሽከራቸው በአገልግሎቱ ተመስግኖ በቤታቸው ስሙ የታወቀ ሰው ነበርና ያንን ያገሩን ባለርስተ ጉልት አቶ በላይ ካሣን አስለቅቆ ጉልቱን እሱ ለመውሰድና ብድሩን ለመመለስ ከብዙ ቀን ጀምሮ በጣም ያስብ ነበረና ለማግኘት ይጣጣር ጀመረ። አስቀድሞም ባላምባራስ አዳል ይኸንኑ የመስፍንነታቸውን አገር ሳይወርሱ ላገርዎ ገዢ የሆኑ እንደ ሆነ፤ ከተወልድኩበት አገር ርስት ጉልት በቀር ሌላ የማስቸግረዎና የምሻው ነገር የለኝም ብሎ ለምኖ እሳቸውንም እሺ አሰኝቶ በማስታወሻ አስጽፎ መዝገብ አስገብቶ ቈይቶ ነበርና በዚያን ጊዜ ነገሩን እያስታወሰ ፍላጎቱ እንዲፈጸም ሥራውን ጀመረ።

አቶ በላይ ካሣ ግን ደጃች አዳል አገሩን እንዳይዙበት እንደሌላው ባለጉልት ሁሉ መታያውን ደኅና አድርጎ አዘጋጅቶ የሰባ ፍሪዳውን ጨምሮ ይዞ ከባላምባራስ አዳል ተገናኝቶ ባልደረባውን ተቀብሎ ሂዶ ነበር። ቢረሳው እዚያ አሽከር መሆኑን ቢያውቅና ሥጋትም ቢኖርበት ካያታቸው ከቅድም አያታቸው ያገኘውን ርስት ጉልት ያለ ትልቅ ጥፋትና በደል እነቀላለሁ ብሎ አላሰበም። ነገር ግን ይኸም ባላጋራው አቶ ቢረሳው ጧት ማታ ጌታው ጥንት የዋሹለትን ነገር እያሰበ በላይ ካሣን ነቅለው ለሱ ርስተ ጉልቱን እንዲሰጡት ጌታውን እጅግ አስቸገራቸው። ደጃች አዳልም ብዙ ጊዜ ይዞት የቈየውን ርስት አቶ በላይ ካሣን ያለምክንያት ነቅለው ለቢረሳው ለመስጠት አሳባቸው ታውኮ ሕሊናቸውም አልፈቅድ ብሎዋቸው ብዙ ጊዜ ነገሩን ችላ እያሉ አቈይተውበት ነበር። ቢረሳው ግን በሌላ አኳኋን ደግሞ ያሰበው እንዲፈጸምለት በወንጀል በኀጢአት አቶ በላይ ካሣን አስከስሶ ብዙ ቀን ያጉላላው ያስቸግረው ነበር። በዚያው ማስረታት

የማይቻል ስለ ሆነበት ሌላ ደግሞ የተንኰል ሥራ ዕይሠራ በተዘዋዋሪ ደጃች አዳልን አይወድም ይጠላል፤ ቢቻለው ሌላም ነገር ለማድረግ አይመለስ እያሰኘ እያስወራ እሳቸው እንደሚሰሙና እንደሚጣሉት ማድረግ ጀመረ። ያ ባላገር ቢረሳው ሠልጥኖ ይኸን ሁሉ ተንኰል ለምሥራት ቻለ። አቶ በላይ ካሣ ምንም በሚከሰስበት ነገር ሁሉ ቢረታም እዚያ በክስ ምክንያት እየመጣ ስለሚጉላላ አንዳንድ የሐሜት ቃልም የተናገራት ብትኖር ያችንም ለደጃች አዳል ያደርሱበት ነበር። ከጥቂት ወራቶችም በኋላ ደጃች አዳል ፈጽመው እንዲጣሉትና እንዲቀየሙት አደረገው። በኋላ ራስ አዳል ተብለው ከጐጃም ጋራ ዳሞትን ጠቅለው መስፍን ሆነው ሲገዙ በነደጃች ተድላ ርስት የተተከሉትን አንዳንድ ሰዎች እየነቀሉ ለሳቸው አሽከሮችና አገልጋዮች ሲተክሉ የአቶ በላይ ካሣም ርስተ ጉልት ነቅለው ለአቶ ቢረሳው ሰጡት።

****

# <u>ምዕራፍ ፪።</u>

በዚያን ጊዜም አቶ በላይ ካሣ አነደድ ከቤቱ ነበርና ይኸንኑ የርስቱን መነቀል ወሬ እንደ ሰማ ትልቅ ኀዘንና ብስጭት ያዘው፤ ያ ገባሩ የነበረ መጥቶ ማጉላላቱና በከበረበትም ቦታ የመዋረዱ ነገር ሁሉ በጣም በርትቶ ተሰማው። በዚህም ምክንያት ስለ ራሱ ኑሮ ወደ ፊት የሚያደርገውን ነገር ለማሰብ ምንም ረጅም ጊዜ ለማግኘት ችሎታ አልነበረውምና ያን ጊዜውን አንድ አሳብ ብቻ ወሰነ። ምንም ቢሆን እንግዲህ በዚህ አገር አልቀመጥም፤ የዚህ አገር ንብረትና ትዳርም አያምረኝም ወደ ሸዋ መሰደድ ነው የሚሻለኝ ብሎ ሚስቱን ወይዘሮ ተዋበችንና ገና ራሳቸውን ያልቻሉ ትልቁ ሰባት፣ ትንሹ አምስት ዓመት የሆናቸውን ሁለት ልጆቹን ይዞ በሌሊት ተነሥቶ ለማንም ሰው ሳያስታውቅ ጠፍቶ ወደ ሸዋ በደጀን በኩል፤ መንገዱን ቀጠለ።

በሁለተኛውም ቀን ጧት ወደ ዐባይ ወንዝ ዳር ደረሰ። ይኸውም መከረኛ ሰው ዐባይ ወንዝ ሲደርሱ ድንገተኛ ዝናም ከወደላይ በጣም ዘንሞ ኖሮ ውሃው ሞልቶ ለመሻገር የማይቻል ሆኖ አገኘው። በዚያን ዘመን በዚሁ መንገድ በኩል የሚያሻግር ድልድይ አልተሠራም ነበርና፣ ይልቁንም በክረምት ውሃው ከሞላ በኋላ የሚተላለፍ መንገደኛ እስከ በጋው ወራት ድረስ አልነበረም። ያቆ በላይ መንገድ ግን ጊዜው ምንም በበጋው ወራት ውስጥ ቢሆን ድንገተኛ ዝናም ስለ ሆነ ቶሎ የሚያልፍ መስሎት ነበርና ሲጠብቅ ጥቂት ከቈየ በኋላ የሚያውቀኝ ሰው ተከታትሎ መጥጦ ያገኘኝ ይሆን ብሎ እጅግ ሠግቶ ነበርና የውሃው ሙላት ጥቂት እንደ መጕደል ሲል አቶ በላይ ደኅና አድርጎ ዋና መዋኘት የሚያውቅ ስለ ሆነ እስቲ በዋና አስቀድሜ እኔ ልሞክረውና እናንተን ደግሞ ተመልሼ አሻግራችኋለሁ ብሎ ልብሱን አወላልቆ አስቀምጦ ለመዋኘት ገባ እየዋኘ ወደ ማዶ ተሻግሮ በደኅና ተመልሶ ደግሞ ሰዎቹን ለማሻገር ሲመጣ እንደ ገና ታልቅ ዝናም ከላይ ዘንቦ ኖሮ ወደ መሓሉ ሲደርስ ድንገት ደራሽ ብርቱ ተጋፊ ፈጣን የሆነ ወራጅ ውሃ ስላገኘው ያንን ጥዎስ ብወዋና ለማለፍ አስቸገረው እንደዚሁ ሲታገል ጥቂጥ በጥቂት እያለ ውሃው አይሎ ከመልካው መሻገሪ አሳስቶ አወረደው። ሚስቱ በርቅ ሁና ትመለከተው ነበርና ውሃው አይሎ እንዳወረደው ስለ አየች ልጆችዋን ካንድ ትልቅ ዛፍ ሥር አስቀምጣ በወንዙ ዳር ለዳር እየሮተች ሄደች፣ በዚያም ሆና የውሃው ሙላት እጅግ በርትቶ እየገፋ ይዞት ሲሄድ እሱም ለመውጣት ሲጣጠር ስለ አየች እየጮኸችና እየተቅበዘበዘች የምታደርገው ነገር ጠፋት። በወንዙም ዳር ለዳር አስቸጋሪውን ቦታ ሁሉ በእንብርኳ እየዳኸች በእጅዋ እየቧጠጫጠች ተከታትላ የባሏን ሁኔታ ብታይ እንደዚያው ለመውጣ እየታገለ ውሃው እያሸነፈው ከዐይኗ እስቲጠፋ ድረ ሙላቱ ይዞት ሲሄድ አየች መሄጃው መንገድ እስኪቸግራት ድረስ ብዙ መንገድ ተከትላ ሄዳ ነበርና በኋላ እዚያው አንድ ቦታ ቆማ እየጮኸች ስታለቅስ ቈየች። የምታደርገውን አጥታ እንደ እብድ ሆና ብቻዋን ጭው ባለ በረሃ ያለ አንድ ዘመድ ወዳጅ ይኸ መከራ ድንገት ስለ ደረሰባት የምታደርገውን አጣች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን እንደ ገና አስተጋብታ ወደ ልጆቿ ለመመለስ መንገድ ብትጀምር ሳይታወቃት የሄደችው መንገድ በጣም ሩቅ ነበርና ቶሎ ለመድረስ

የማትችል ሆነች። እግሩዋም ሁሉ በየዕንቅፋቱ ቈስሎ ድካም ስለ ተሰማት ካንድ ጥላ ሥር ዐርፋ ቈይታ ነበርና ገና ከልጆችዋ ሰንድ ሳትደርስ ብዙ መንገድ እንደ ቀራት ከጐጃም ወደ ሸዋ የሚሄዱት ሁለት መንገደኞች ቅድም ተከተል ሆነው በስተደጀን መልካ ወደ ዐባይ ወንዝ እንደ ደረሱ እነዚያን ሁለት ልጆች ሲያለቅሱ አንድ ዛፍ አጠገብ አገኙዋቸ። እነዚሁም መንገደኞች ለልጆቹ ሰው እንዳላቸው ብለው በዙሪያው ቢመለከቱ አንድም ሰው ለማየትና ለማግኘጥ አልቻሉም። ቢጣሩም የሚመልስላቸው አላገኙም የታሰሩ ከብቶችና ጥቂት የተቋጠረ ሥንቅ ብቻ ከልጆቹ አቅራቢያ ነበር ልጆቹንም ቀርበው ቢጠይቁዋቸው በልቅሶ ድምፃቸው ተዘግቶ ነበርና ምንም የተካከለ መልስ ሊስጡዋቸው አልቻሉም።

መንገደኞቹም እየተዛወሩ ሰው ፈልገው ካጡ በኋላ ያመጣቸውን ሰው ውሃ ወስዶት ይሆናል በማለት እየዞሩ ሲመለከቱ ከድንጋይ ላይ ልብስ ተቀምጦ አንደኝው አየና ሄደው አንሥተው ቢመለከቱት የወንድ ሙሉ ልብስ ሆኖ ስላገኙት እንዳሰቡት ሁሉ ለመዋኘት ገብቶ ያመጣቸውን ሰው ውሃው እንደ ወሰደው ያረጋገጡ መሰላቸው። ስለ ልጆችም አስበው ሰው ወደ አለበት መንደር እንዳንወስዳቸው አጠገባችን ከቅርብ መንደር ያለ መንደር የሚገኘው ዳገቱን ወጥተን ከሩቅ ሄደን ነው። እክዚህ በረሃ ላይ እንዲያው ለአውሬ ትተናአቸው ከምንሄድ ይዘናቸው ብንሄድ ይሻላል ብለው ተነጋገሩ። ያን ጊዜም ውሃው መጕደል ጀምሮ በከብት ያሻግር ነበርና ትልቁን ልጅ አንዱ፤ ትንሹን ልጅ ሁለተኛው መንገደኞች በከብት ላይ አድርገው ወንዙን አሻግረው ይዘዋቸው ሄዱ።

እናታቸውም ስለ ባለቤቷ በኀዘን በለቅሶ ስትቀጠቀጥ ውላ እየወደቀች እየተንሣች መጥጣ ልጆቿን ከተወችበት ቦታ ብትደርስ አንዳቸውም የሉ፤ ወዲያም ወዲህም እየሄደች ብትፈልጋቸው ልታገኛቸው አልቻለችም፤ እንደ ገናም ለቅሶዋን ቀጥላ ትጮህ ጀመረች፤ ምንም ኀዘንዋን የሚያጥናናት ነገር አልነበረም። ምናልባት አውሬ በልቷቸው ይሆን ብላ በዙሪያው የፈሰሰ ደም እንዳለ ብትሻም አላገኘችም።

ጥቂት ከቈየች በኋላ ወደ ማዶ ዓግራ ብትመለከት ሁለት ባለ ከብቶች ሰዎች ተሻግረው ዳገቱን ሲወጡ ከመንገዱ ላይ በርቁ አየች፣ ያን ጊዜም

ምናልባት እነዚያ ሰዎች ወስደዋቸው ይሆን፣ ብላ ጠርጥራ ነበር። ውሃ በእግር ለመሻገር አይቻልም ነበርና ተከታትላ ሄዳ እርግጡን ለማወቅ የማትችል ስለ ሆነች የምታደርገው ዘዴ (መላው) ጠፍቶዋት ያንኑ ለቅሶዋን እያለቀሰች አንዳንድ ጊዜም ባገሯ የልቅሶ ዜማ እያንጐራጐረች በአንድ ድንጋይ ላይ ተቀምጣ ዕንባዋን እንደ ውሃ ታፈሰው ነበር።

## እንጉርጉሮዋ።

ትልቁ ጀማችን ወንዛችን ዐባይ፣
አንተም የኛን ጉዳት መውደድህ ነው ወይ።
አምላክ ምናጠፋሁ ከሰው የበለጠ
ወረደብኝ ቍጣህ ሁሉም ተለወጠ።
ዐውቃለሁ ብቻዬን ከሆድ እንደ ወጣሁ
እንጃ አሁን መቻሌን የማውቀውን አጣሁ።
ባንድ ቀን አካሌ ልጆቼስ የት ሄዱ፤
አትናገር ቃሌ አላለቀም ጉዱ።
የት ነው አሁን ያለሁ እኔ ከርታታዋ፤
እዚህ ቀርቻለሁ ወዬው ጉደኛዋ።
እንግዳ ነገር ነው፣ በእኔ የደረሰ፤
ኑሮዬ በመላው ባንድ አፍታ ፈረሰ።
ለምን እዚህ ቀረሁ ሴቲቷ ብቻዬን፤

ደግሞስ ሊታሳየኝ ወደምትሄድበት ቦታ ቸግሮዋትና ጨንቆዋት ካንዱ ወደ አንዱ እየሄደች ወደየቍጥቋጦው ሥርና ወደዋሻው እየሮጠች ድንገት ልጆችዋን የምታገኝ እየመሰላት ብትፈግል ምንም አጣች። በልቅሶና በጩኸትዋ ብዛት ሰውነትዋ መዛል መድከም ጀመረ። ጊዜውም እየተማሸ ሄደ። በእመቤትነት የኖረች ሴት ይኸ ሁሉ አደጋ ድንገት ባንድ ጊዜ ስለ ደረሰባት፤ በብርታት ለመቃወም የማትችለው ሆነ። ያለቀሰችበት ዐይኗ

አብጦ የጮኸችበትም ድምፁዋ ተዘግቶ የባሉዋን መጨረሻ ኢያለሁ በማለት ስትከታተል የሄደችውም ጥሻውን ሁሉ እየጣሰች አንዳንዱንም አስቸጋሪ ቦታ መንገድ ስለ ሌለው በጕልበትዋ እየዳኸች ነበረና እጅና እግርዋ ሁሉ ተላልጦ፣ ቈስሎና አብጦ አእምሮዋን ስታ በዚያ በረሃ ካንድ ዛፍ ሥር ወድቃ በሞትና በሕይወት መሓል ተዘረጋች።

ጌታው አልዩ የሚባል አንድ የወሎ ሰው ለጕዳዩ ወደ ጐጃም መጥጦ ሰንብቶ ነበረና በዚሁ ቀን ተመልሶ በሸዋ በኩል ወደ አገሩ ለመሄድ ስለ መጣ እዚሁ ዐባይ ከደጀን መልካ ዳር ሲደርስ ጊዜው ስለ መሸበት ከዚሁ አድሬ ነገ ጥዋት እሻገራለሁ ብሎ አንድ ጥግ ቦታ ሰፈሩን አደረገ። ሁለት አሽከሮች የተከተሉት ነበርና ሰፈር ከሆነ በኋላ ደረቅ ዕንጨት ለቃቅመው፤ እሳት አንድደው ራት ለማሰናዳት እልፍ ብለው ሄደው ጭራሮ መሳይ ሲሰበስቡ ጊዜው መሽቶ ድንግዝግዝ ብሎ ለዐይን በጣም አይታይም ነበርና በድንገት ካንድ ዛፍ ሥር የወደቀ ነገር አዩ። ባዩትም ጊዜ ድንጋይ ነውን ወይስ ዕቃ እያሉ ዝግ ብለው ቀርበው ቢመለከቱ የወደቀው ሰው መሆኑን ዐወቁ። ለገንዘቡ ሲል ሽፍታ የገደለው መስሏቸው ደንግጠውና ፈርተው ወደ ጌታቸው ወደ አቶ አልዩ ዘንድ ተመልሰው ሄደው ኧረ እዚያ እይሞተ ሰው ወድቆ ስላገኘን ልንነግርዎ ነው የመጣን ሽፍታ ገድሎታል ይመስለናል ከዚያ ከዛፉ ሥር ተዘርግቷል እያሉ በጣታቸው እያመለከቱ ስለ ነገሩት ለጊዜው እሱም ደንገጥ ብሎ ጥቂት ከቈየ በኋላ፤ እሱም ከዚያው ሄዶ አይቶ ነገሩን ለመረዳትና ለማወቅ ስለ ፈቀደ ጊዜው በጣም መሽቶ ነበርና ፋና አስበርቶ አሽከሮቹን አስከቶሎ ሄዶ ቢያይ አንዲት ሴት ወድቃ ተዘርግታ አገኛት፤ እንደ ደረሰም አሽከሮቹ እንደ ነገሩት የሞተች መስላው ነበር፤ በትር መሳይ ይዞ ነበረና በበትሩ ጫፍ ነካ ነካ እያደረገ ሲመልከት ጥቂት ስትንቀሳቀስ አየ፤ ወዲያውም ተነሺ ተነሺ ምን ሆነሽ እዚህ ወድቀሻል እያለ ቢጠይቃት ድካም በዝቶባት ድምፁዋ ተዘግቶ ነበረና ምንም መልስ ልትሰጠው አልቻለችም። ዐይንዋ ግን ጥቂት ገርበርብ ብሎ ወዲያ፥ ወዲህ እየተንቀዋለለ ሲመለከት ስለ አየው ርዳኝ መከረኝዋን ሴት የምትል መስሎ ለሕሊናው የኀዘን ስሜት ስለ ሰጠው ከዚህ አጕል ቦታ ወድቃ አውሬ ደግሞ እንዳይበላት ብሎ አስቦ ወደ ሰፈሩ ለመውሰድ ደጋግፎ አንሥቶ በእግሯ

ለመሄድ የማትችል በመሆንዋም አሽከሮቹ ተጋግዘው እንዲወስድዋት አድርጎ እሱም እየረዳ ተሸክመው ወደ ሰፈሩ ወስደው አደረሱዋት። እዚያምሣር መሳይ አጫጭደው ጐዝጉዘው) አስተኙዋት፤ ጥቂት ከቈየችም በኋላ ውሃ አጠጥተው ራትም እንድትበላ አቅርበውላት ነበር ነገር ግን ጉሮሮዋ ለመዋጥ ስላልቻለ እኽል ለመብላት አልሆነላትም ነበር።

ወዲያው ተልባ በማር በጣብጠው ስለ ሰጧት ነፍስዋ መለስ ብሎ ትንፋሽዋን እንደ ልቧ መተንፈስና ጥቂት ጥቂትም መናገር ቻለች። በዚያም ወድቃ በነበረችበት ቦታ ብቻዋን በመሆንዋና የጨለማውም ግርማ ተደርቦ ከድካምዋ ጋራ ተጫኑዋት ቢያስጨንቃት ያገኛትም ሐዘን ልቡዋን ቢያቈስለው በኋላ ረዳት ሰው በማግኘቷ ጥቂት ቀለል አላት። ስለሆነም የሆነውን አደጋ ባሰበችው ቍጥር ምንም ሳትናገር ዕንባዋ እየፈሰሰ ይወርድ ነበር። ጌታው አልዩም ድካምዋንና ሁኔታዋን ሁሉ ስላየ፣ ያን ጊዜም ያገኛትንና የሆነችውን ነገር ለመጠየቅ አልፈለገም። ልብስ ሰጥጦ ዐርፋ ተኝታ እንድታድር አደረገ። በማግሥቱም ጡዋት አቶ አልዩን ስለዚች ሴት ነገር ትልቅ አሳብ ያእው፤ ሰው ወዳለበት ወደ መንደር ወስዶ እንዳያደርሳት መንደር የሚገኘው በጣም ሩቅ ሂዶ ያውም ወደ ኋላው ተመልሶ ሆነበት። ከዚያም ትቶዋት እንዳይሄድ እጅግ አሳዘችው ደግሞም አንድ አደጋ ያገኛት ይሆናል ብሎ አሰበ። በዚሁም ጥቂት ሲቸገር ቈይቶ ለሁሉም ነገር የምን ሴት እንደ ሆነችና የምትሻውንም እሱዋኑ ብጠይቃት ይሻላል ብሎ ወደ እሱዋ ዘንድ ሄዶ አንንቺ ሴት የመጣሽው ከወዴት ነው፤ ያገኘሽስ ነገር ምንድነው፤ አሁንስ ለመሄድ የምታስቢው ወዴት ነው ብሎ ስለ ጠየቃት እሱዋም ሌሊቱን ዐርፋ ስላደረች ያን ጊዜም በደኅና ለመናገር ችላ ነበርና የመጣችበትን ምክንያት ሁሉንም በዝርዝሩ ለመናገር ሳትፈቅድ፤ የመጣሁት ከባሌና ከልጆቼ ጋራ ከሩቅ አገር ነው፤ ለመሄድም ያሰብነው ወደ ሸዋ ከተማ እንጦጦ ወደሚባለው ነበር። ትናንት ከዚህ እንደ ደረስን ውሃው ሞልቶ ስላገኘነው እስቲጐድል ድረስ ስንጠባበቅ ቈይተን ጥቂት መጉደል ሲጀምር ባሌ አስቀድሞ በዋና ለመሞከር ገብቶ ውሃውም አይሎበት ከመልካው አሳስቶ እያወረደ ይዞት ሲሄድ አየሁ ያን ጊዜም በጣም ደንግጬ ካሁን ይወጣ ይሆን እያልሁ በወንዙ ዳር ዳር

እየተከታተልኩና እየሄድሁ ስመለከት ውሃው እየባሰ አሸንፎት ይዞት ሄደ። ወደዚያውም ስሄድ ሁለቱን ልጆቼን ከዚያ ከዛፍ ሥር ትቻቸው ነበርና ብመለስ ደግሞ ሁለቱንም ልጆቼን አጣኋቸው ወዲያ ወዲህም እየሄድሁ ፈልጌያቸው ነበር አላገኘኋቸውም አውሬም በልቷቸው ወይም ሰው ወስዷቸው እንደሆን አላወቅሁም ነገር ግን ባሌን አጥቼ ስመለስ ወዲያ ማዶ ተሻግረው የሄዱ ባለከብቶች ሰዎች እዳገቱ ላይ ርቀው አይቼ ነበርና ልጆቼን ፍልጌ ካጣኋቸው በኋላ እነዚያ ሰዎች ወስደዋቸው ይሆን በማለት ልቤም ጠርጥሮዋል። በእግሬ ተሻግሬ ለመከታተል የማልችል ስለ ሆንሁ ይኸ ሁሉም አደጋ ድንገት ስላገኘኝ ሐዘንና የልቅሶ ጩኸት ሰውነቴን አቀኀስሎት የማደርገውን ነገር አጥቼ አእምሮዬ ሁሉ ጠፍቶ እግዚአብሔር አትሙች ብሎኝ ኖሮ እወደቅሁበት ያገኛችሁኝ በዚህ ምክንያት ነው እያለች ዕንባዋን እያፈሰሰች ነገርዋንም አንዳንድ ጊዜ እያቋረጠች ነገረችው።

ጌታው አልዩም ነገሩዋን በትዕግሥት ሰምቶ ባገኛትም መከራ አዝኖና ተከዞ ጥቂት ከቈየ በኋላ አሁንስ እንግዲህ የምትሽው ምንድነው በሚቻለን እንድንረዳሽ ብሎ ስለ ጠየቃት ወደ ጐጃም ለመመለስ አልሻም ውሃው በጣም እንደ ጐደለልኝ ተሻግሬ ምናልባት እነዚያ ያየኋቸው ባለበቅሎዎች እንደ ሆኑ ልጆቼን የወሰዷቸው እነሱ የደረሱበትን ወሬ እየጠየቅሁ እስካገኛቸው ወይም በችራሽ ልጆቼ መጥፋትቸውን እስካወቀው ድረስ ለመፈለግ ነው። የባሌን ቀኀርጥ ነገር እዳወቅሁ እስካገኛቸው ወይም በጭራሽ ልጆቼ መጥፋታቸውን እስካውቀው ድረስ ለመፈለግ ነው። የባሌን ቀኀርጥ ነገር እንዳወቅሁት የነሱንም መጨረሻ ለማወቅ ነው የምሻው አለችው።

አቶ አልዩም ምናልባት ተሻግረሽም ቢሆን ልጆችሽን አላህ ቢያስገኝልሽ ወደ እንጦጦስ ሄደሽ የምታውቂው ሰው ዘመድና ወዳጅ ከዚያ አለሽን? ብሎ ስለ ጠየቃት ባሌ ነበር ሁሉንም የሚያውቅ እኔስ ምንም የማውቀው ሰው የለኝም። ልጆቼን ቶሎ ባገኛቸው ከዚያ ወዲያ ደግሞ ወደምሄድበት አስባለሁ አለችው።

አቶ አልዩም እጅግ አዝኖላትና አስቦላት እንደዚህ አለ ዋናው ፈቃዱ እኛ ወደምንሄድበት ተሻግሮ ለመሄድ ከሆነ እኛም አብረን ልጆቿ ቢገኙ እናፋልጋታለን ባይገኙም ፈቃድዋን ደግሞ ጠይቄ አሰበችው ቦታ አድርሼ እሄዳለሁ እንጂ፤ እዚህ ለማን እተዋታለሁ ብሎ አስቦ ወዲያውም ለሱዋ እንደዚህ ከሆነ አሳብሽ ወንዙንም እኛው አሻግረን ልጆችሽንም እኛ እናፋልግሻለን አላት። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብላው አብራው ለመሄድ ተነሣች። እሱም ወንዙን በደኅና በከብት አሻግሮ አብረው የመንገዳቸውን ጉዞ ያዙ ዳገቱን ወቶ ጃርሶ ከሚባለው አገር ሲደርሱ ሰፈር አደረጉ። በየመንገዱ የሚያገኙትን ሰው ሁሉ የሚጠይቁት ሁለት ልጆች ይዘው የሚሄዱ ሰዎች አግኝታችኋል ወይ እያሉ ነበር።

ነገር ግን አየን የሚል ከመንገደኞች ባለማግኘታቸው አዝነው እዚህ ጃርሶ እሰፈራቸው አንድ ቀን ደግሞ ውሎ አድርገው መንደረኛውንና አንዳንድም መንገደኞች ሲጠይቁ ውለው አንድም ምልክት ሳልላገኙ ተስፋዋ እየደከመ እንደገና ደግሞ ታዝን ታለቅስ ጀመረች።

ጌታው አልዩም እመቤት ሴት እንደ ነበረች ባኳኋና ሁሉ እየገመተና እያየ እጅግ ያዝንላት ከሐዘኑዋም ለማጥናናት ይሞክር ነበር። እሱዋ ግን አሳቡዋ በጣም በሐዘን ስለ ተነካ የሚናገረውንም ሳታስተውለው እንዲያውም አንዳድን ጊዜም እሱዋን ያገኘ አደጋ ሌላውንም ሰው ሁሉ ያገኘ እየመሰላት ሰው ሲሥቅና ሲጫወት ስታይ ይገርማት ነበር። በማግሥቱም ከጃርሶ ሰፈራቸው ተነሥተው መንገዳቸውን ቀጥለው ሲሄዱ በየመንገዱ የሚገኘውን ሰው ሁሉ የሚጠይቁ የነዚህኑ የልጆች ነገር ነበር፤ ወሬያቸውን ግን ምንም ለማግኘት አልቻሉም።

****

# ምዕራፍ ፫።

ልጆችዋም ትልቁ ካሣሁን ትንሹ ጌታነህ ይባሉ ነበር። ትልቁ ልጅዋን ካሣሁንን አሻግሮ ይዞት የሄደ አቶ ደባይ የሚባል የሸዋ ሰው አገሩ ባሶ ሥራው ጨዋ ወታደር ባለሪም ነበርና ልጁን ይዞ እንደ ተሻገረ ማርያም አጠገብ ከመንገድ ራቅ ባለ ቦታ አንድ ባለ ርስት ዘመድ ነበረውና እዚያ ደርሶ ለመሄድ ሌቱን ሁሉ በችኰላ ሲሄድ አድሮ ወደዚያው ጐራ ብሎ ደርሶ ጥቂት ቀኖች ሰንብቶ ወዳገሩ ሄደ።

ደግሞ ትንሹን ልጅ ጌታነህ የሚባለውን ይዞት የሄደው አቶ ዲንቃ የሚባል የጉራጌ ነጋዴ አገሩ አገምጃ ከሚባለው ወረዳ ውስጥ ነበርና የጎሐ ጽዮንን ዳገት እንድ ወጣ ዋናውን የሸዋውን አውራ ጐዳና ትቶ በግንደ በረት በኩል አድርጎ ነበርና የሄደው ስለዚህ እናታቸው እንዳሰበችው ባውራው በሸዋ ጐዳና ከሚመጡት መንገደኞች ወሬያቸውን ለማግኘት አልቻለችም ነበር። አቶ አልዩ ግን እሱዋኑ ይዞ እግረ መንገዳቸውን ፍቼ ከተማና ደብረ ሊባኖስም ገዳም በደረሱ ጊዜ ልጆቹን መፈለጋቸውንና ወሬ መጠየቃቸውን አልተውም። ነበርና ምንም ለማግኘት አልቻሉም። እናታቸውም በጣም ተስፋ መቍረጥ ጀመረች። የምትፈልግበትን አገር የምታገኝበትንም ምልክት ለማወቅ ቸገራት። እንጦጦም ከተማ ከደረሱ በኋላ ጥቂት ቀን እዚያው ዐርፈው ሰንብተው ሳለ አንድ ቀን አቶ አልዩ ለወይዘሮ ተዋበች እንግዲህ እዚህ አደረስሁሽ ልጆችሽንም እስከ ዛሬ ፈልገን ማግኘት አልቻልንም አሁን እዚህ እንደ ምን ሆንሽ ለመኖር ትፈቅጃለሽ የምታውቂው ሰው ያለ አይመስለኝም እኔ ወዳገሬ ወደ ወሎ መሄጃዬ ጊዜው ደርሶዋልና የምታስቢውን ባውቀው እወዳለሁ ብሎ ስለጠየቃት እሷም እኔ በዚህ አገር የማውቀው ሰው የለኝም እንዲሁ እየለመንሁ ቈይቼ ለሥራ ገረድ የሚቀጥር ሰው ባገኝ የምችለውን እየሠራሁ እግዚአብሔር እንደ ፈቀደልኝ አድራለሁ ሌላ ምን ለማድረግ እችላለሁ፤ አንተም እስካሁን ስለ ረዳኸኝና ስለ ደከምህልኝ እግዚአብሔር የመልካም ሥራ ዋጋህን ብድሩን ይክፈልህ አለችው። አቶ አልዩም ከጥቂት ቀኖች ወዲህ ስለርሱዋ ሲያስበው የቈየ ነገር ነበረውና ወዲያውም ነገሩን ገልጦ የምታውቂው ሰው እዚህ አገር

ከሌለሽ እንዲያው እዚህ ከመጉላላትሽ ፈቃድሽ ቢሆን እኔም ብቻዬን ያለሁ ሰው ነኝና ከኔው ጋር ሄደሽ አብረን ብንረዳዳ እወድ ነበር ብሎ በትልቅ አክብሮት ፈቃድዋን ስለ ጠየቃት ባሳቡም ሚስት ለማድረግ መፈለጉን ስለ ተረዳችው ለጊዜው ጥቂት ደንገጠች ያገኛትን የመረረውን የሐዘን መከራ ተደራርቦ የደረሰባትን እያሰበች ከምትወደው ባልዋ ተለይታ ልጆችዋን ሁሉ አጥታ እንደ ገና ደግሞ ባል አግብታ ቤት ንብረት ከሌላ ሰው ጋራ ይዛ ደስ ብሎዋት ለመኖር ምንም ልጅ እግር ሴት እንኳን ብትሆን አሳብ አልነበራትም። አንዳንድ ጊዜም መንና ወደ ገዳም ለመሄድም ትፈልግ ስለ ነበረ፤ በዚህ በጥያቄው እጅግ ተቸገረች። እንቢ እንዳትለው ተቀጥራ እየሠራች ለማደር እንደ ሆነ ፍላጎትዋን አስቀድማ ገልጣ ስለ እንገረችው ደግሞም ከወደቀችበት አንሥቶ አስታሞ ልጇቿን በመፈልግም ሁሉ ከልብ የረዳትን ሥራውን ሁሉ አይታለችና ያንን ሁሉ እያሰበች የጠየቃትን እንቢ ብላ ማሳስዘንም የማይገባ ውለታ ቢስነት መሰላት። እንደዚሁም በሁለት አሳብ መኻል ተቸግራ ጥቂት እንድ እቈየች አንድ ምክንያት ደግሞ አገኘች።

ይኸውም የወሎ ሰው መሆኑን ስላወቀችና አንዳንድ ጊዜም አላህ እያለ ሲናገር ሰምታው ነበርና እስላም ይሆናል ብላ ጠርጥራ ይኸንኑ ሰበብ በማድረግ እኔ የክርስቲያን ልጅ ክርስቲያን ነኝ ስለዚህ ሌላ ሃይማኖት ካለው ሰው ጋራ አብሮ ለመኖር እንዴት ይሆንልኛል ብላ መልስ ሰጠችው።

እሱም እሱዋን ደስ አሰኝቶ አሳቡ የተፈጸመለት መስሎት እኔ ባጼ ዮሐንስ ዘመን ክርስትና ተነሥቻለሁ ክርስቲያን ነኝ አላት።

እሷም የክርስትና ስምህ ማነው ብላ ስሙን ለማወቅ ጠየቀችው። እሱም ያን ጊዜ ባዋጅ ያገኘውንም ስም ዘንግቶት ረስቶት ኖሮ እንዲያው አፉ እንዳመጣለት ወለተ ገብርኤል ነው አላት።

«ማናቸውም የመከራ ሐዘን ከዋለ ካደረ እየተረሳ እየተዘነጋ መሄድ በሰውነት ያለ ጠባይ በመሆኑ» የሴት ስም ስለ ነገራት እንደ መሣቅ ፈገግ አለች። ግን ልታሳፍረው ስላልፈለገች የሴት ስም መሆኑን አልነገረችውም፤ ብቻ እውነትም ያዋጅ ክርስቲያን ኖረዋልና አለችው።

«አጼ ዮሐንስ በውነት የታወቁ ስመ ጥሩ ክርስቲያን ስለ ነበሩ፤ የክርስቲያን ሃይማኖትንም አብዝተው ስለሚወዱ በዘመናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላው ክርስቲያን እንዲሆን ፈቃዳቸውና ምኞታቸው ነበርና ስለዚህ በውድም ሆነ በግድ ዐዋጅ ዐውጀው እስላም የሆነ ሁሉ ክርስቲያን እንዲሆን አዘው ነበር። ያን ጊዜም በፍርሀት ያለ ትምህርትና ያለ መረዳት ክርስትና የተነሣ ይልቁንም በወሎ ብዙ ስለ ነበረ አቶ አልዩም ከነዚያ አንዱ ኑረዋል።»

ወይዘሮ ተዋበችም ጥቂት እያሰበች ቈይታ ነገሩን አውጥታ አውርዳ ተመልክታ ከዚህ ከማላውቀው አገር ብቻዬን ቀርቼ የሚደርስብኝንና የሚያገኘኝን ነገር አላውቀውምና በመከራ ጊዜ የረዳኝን ከወደቅሁበት ቦታ ከሞት አፋፍ ያነሣኝን እምቢ ብዬ ከማሳዝነው ፈቃዱን ፈጽሜ ለክርስቲያንነቱም በአጤ ዮሐንስ የተፈለመ ከሆነ እኔም እውነተኛ ክርስቲያን እንዲሆን እጥራለሁ በምግባርም በኩል መልካምነቱን ያየሁት ስለ ሆነ ክርስቲያን ነኝ ብሎም በአንደበቱ ስለ ተናገረ፣ ወደ ኋላ የሚመለስ አይመስለኝምና ከሱ ጋራ አብሮ መኖር ይሻለኛል ብላ በዚሁ ፈቃዷን ወስና ክርስቲያን ከሆንክ እሺ አለችው።

አቶ አልዩም ምንም ካገኛት ጥቂት ጊዜም ቢሆን የሃይማኖቷን ብርታት የሰውነቷን መልካምነት የመልኳን ውበት እያደር እየበረታ አይቶዋት አፍቅሮዋት የሚያከብራትና የሚመለከታት እንደ እመቤት ነበርና የሱዋን የእሺታ ፈቃድ በማግኘቱ በጣም ደስ ብሎት ወደ አገሩ ወሎ ይዞዋት ሄደ። ቤቱም ቦሩ ሜዳ ከሚባለው አገር ነበር።

ያ ያቶ በላይ ካሣ የሚባለው ሰው ያባይ ውሃ ሲወስደው ሚስቱ ከወንዙ ዳር ለዳር እየተከተለች ሙላት ውሃ ይዞት ሲሄድ ለዐይኗ እስኪጠፋ ድረስ ተመልክታው የነበረው የውሃውን ሙላት በመዋኘት እየታገለ ብዙ ርቆ ከሄደ በኋላ አንድ ትልቅ የጒርጒ ዛፍ ግንድ የሰዎችና የከብት ሬሳ ሙላቱ ከላይ ይዞት ሲመጣ በወንዙ መኻል እየተንሳፈፈ ሲሄድ ድንገት አግኝቶ እየዋኘ እንደ ምንም ተጣጥሮ ሄዶ ቀርቦት ግንዱን አግኝቶ

ስለያዘው እሱን በመደገፍ ጥቂት ፋታና ዕርፊት እያገኘ ከዚያም ግንድ ጋራ አብሮ እንደዚያው ብዙ ሄደ።

ያንኑም ግንድ በመጥፎ ቦታ ላይ ሲደርስ እየለቀቀ ሲዋኝ ከደኅናው ቦታ ላይ ሲይዝ ወንዙ አጠፍ ብሎ ከሚሄድበት አንድ ገመገም ቦታ ሲደርስ እሱ ተደግፎት የነበረውን የዛፍ ግንድ በኀይል ውሃው ከላይ ስለ ገፋው ወደ ገመገሙ ወንዝ ዳር መሬቱን ወግቶ ስለ ተጋዳና ስለ ቆመ በዚያ በኩል በየብሱ መሬት ላይ የበቀለ ያንድ ትልቅ ዛፍ ቅርንጫፍ ክንፉ ወደዚያው ወደ ወንዙ የተዘረጋ በማግኘት አቶ በላይ ተጣጥሮ ያንን ይዞ በብዙ ችግር ከወንዙ መውጣት ቻለ።

የወጣበትም ቦታ በወዲያ ማዶው ወገን ግንደ በረት በሚባለው አገር ላይ ነበር። እዚያም እንደ ወጣ ራቁቱን ስለ ሆነ ቅጠል መሳይ ቄራርጦ በሣር እያይዞ አሳስሮ የመጀመሪያው ሰው አዳም ከገነት ሲወጣ የለበሰውን ዐይነት ቅጠል ለብሶ አንድ ለምርኩዝ የሚሆን በትርና የሚሄድበትንም ጥሻ የሚገላልጥበት ከዛፉ ገንጥሎ ይዞ በዚያ እየገላለጠ ሰው ወደሚገኝበት መንደር ለመድረስ አስቦ መሄድ ጀመረ። ውሃው ሲያንገላታው እየዋኘም ሲታገል የዋለበት አካላቱ ቈሳስሎ እግሩንም ዛፉ አማትቶት ኖሮ የሚሄደው እያነከሰ ነበር። በዚሁም ላይ ጥርጊያ መንገድ ስላላገኘ አንዳንድ መጥፎ ቦታ እያጋጠመው በእምብርኩ እየዳኸ በጁ እየቧጠጠ ብዙ መንገድ ሄደ። ዋናውም ሐሳቡ አንዲት ስላች መንገድ እንኳ ቢሆን አግኝቶ በዚያች እየሄደ ምኞቱ ሰው ውወዳለበት ለመድረስ ስለ ነበረ ያችኑ ስላች መንገድ እስኪያገኝ ብዙ ድካምና ልፋት አገኘው።

ወዲያውም ጊዜው እየተማሸ ስለ ሄደ ምንም ብዙ መከራ ያሳለፈ ጐበዝ ሰው ቢሆን፤ ይኸ ድንገት የደረሰበት አደጋ በጣም መጕላላት አብዝቶበት ሰውነቱ ስለ ደከመ ፍርሀት ተሰምቶት ባጠገቡ አንድ ነገር ኰሽ ኰሽ ባለ ቍጥር ይደነግጥ ነበር፤ በዚያችውም ባገኛት አንዲት ስላች መንገድ እንዲሁ እየወደቀ እየተነሣ ሲሄድ በጣም ጊዜው እየመሸና እየቸለመ ሄደ። የጊዜውም መጨለምና መምሸት ለመከራው ተጨማሪ ስለ ሆነበት አንዳንድ ጊዜም ያችኑ ስላች መንገድ እየሳተ፤ እየተደናገረውም እየቆመም በጣም ተቸገረ፤ ያችን ስላች መንገድ በማግኘቱም ሰው ወዳለበት ታደርሰኝ

ይሆናል ብሎ ያደረገው ተስፋው ተበላሸበት የሚያደርገውም ነገር ጠፍቶት እንዲያው ቆሞ ሲጨነቅ በድንገት ከሩቅ በምሥራቅ ወገን የነደደ እሳት ብርሃን ነበልባሉን አየ፤ ያን ጊዜም ጥቂት ላሳቡ ቀለል ብሎት ይኸ የሚታይ የሩቅ እሳት የነደደው ያለጥርጥር አጠገቡ ሰው ቢኖር ነው፤ ወደዚያው ፊት ለፊት አቅንቼ ብሄድ ነው የሚሻለኝ ብሎ ያንኑ እየተመለከተ በዚያው አቅጣጫ እየወደቀ እየተነሣ በብዙ ችግር እየሄደ አገሩም በረሃ በመሆኑ በግራ በቀኙ ያውሬ ድምፅ እያስራራው፤ አንዳንድ ጊዜም የሚያየው የሩቅ እሳት ለመጥፋት እንደ መድከም ሲል አቅጣጫው ጠፍቶ ሊሳሳተኝ ነው እያለ ባሳቡ ሲጨነቅ የእሳቱ ብርሃን ጸዳል ግን ከፍ ከፍ ብሎ ሲይይ አሳቡ እየተበረታታ በብዙ ችግር ከሌሊቱ ወደ ስድስቱ ሰዓት ሲሆን እዚያው ካየው እሳት አጠገብ ለመድረስ ቻለ ያም እሳት የነደደበት ቦታ ወደ ሸዋ የሚሄድ አንድ ትልቅ ነጋዴ የሰፈረበት እሳቱም ከብት የሚጠብቁ ጐረመዳኞች ያነደዱት ኑሮ እሳቱንም እየሞቁ ከብት የሚጠብቁት አለመንገድ በሌላው ወገን የኰሽ ኰሽታ ድምፅ ስለ ሰሙ፤ ሌባ መጣ እያሉ ዱላቸውን ይዘው እየተጯጯሁ ወደዚያ መከረኛ ሰው ሄዱ። እሱም ሲመጣ አኳኋናቸውን ስላየ ለመሸሽ ከጀት ነበረ። እንነገር ግን አልቻለም፤ ደረሱበት ሌባ አለመሆኑም ለመናገርና ለማስታወቅ ቢሞክር በጩኸታቸው ብዛት የሚሰማው አላገኘም።

ቢሰሙም የሚያምኑት አለመሆናቸውን ዐወቀው። እንዲሁም ደርሰውበት በዱላ እየነረቱና እየመቱ ይዘው እጆቹን በገመድ የፊጥኝ አስረው ወደ ሰፈሩ እሳት ወዳለበት ወስደው ቢመለከቱት ራቁቱን የሆነ ቅጠል መሳይ ሽልሎ የታጠቀ አከላቱ የቈሳሰለ ሰው ሆኖ ስለ አዩት ከሌላ ዘንድ ለመስረቅ ሂዶ የተደበደበ ሌባ መስሎዋቸው እሱም እሱም አንዳንድ ነገር ለመናገር አስቦ እንደማይሰሙት ዐውቆ ዝም አለ። በዚሁም በሆነው ጫጫታ የሰፈሩ ሹም ዋናው ነጋዴ ከመኝታው ነቅቶ ነበርና ተነሥቶ ልብሱን ለባብሶ እነሱ ወደ አሉበት እሳት ዘንድ ቢሄድ ሌባ ይዘናል ብለው እዚያ እየደበደቡ ሲያጕላሉት አየ። ነጋዴውም ጨዋ ሰው ለሰው ርኅራኄ ያለው ነበርና ምንም ጐረደማኞቹ እንደ ነገሩት ለጊዜው ሌባ መስሎት እንኳን ባያምንም ያለ ደንብ እንዲመቱትና እንዲያጕላሉት

አልፈቀደላቸውም። እንዲያውም ወደሱ እንዲቀርብ አድርጎ በፊት ጋላ መስሎት በጋልኛ ቋንቋ የምን ሰው ነህ ከወዴት ነው የመጣኸው ብሎ በርጋታ ጠየቀው።

እሱም በአማርኛ ቋንቋ የዚህ ዓለም መከራ ከማረከው ሰው አንዱ ነኝ እነሱ እንደሚሉኝ ሌባ አይደለሁም። በደጀን መልካ ላይ ላይ ያባይን ውሃ በዋና ለመሻገር ስሞክር የውሃ ሙላት ደርሶብኝ ከመልካው አሳስቶ አውርዶኝ ከዚያ ከሩቅ ቦታ እየታገልሁና እየዋኘሁ ለመውጣት ስፍጨረጨር ቈይቼ እግዚአብሔር ቈይ አትሙት ብሎኝ ኖሮ ውሃ አንሳፎ ይዞት የሚሄድ አንድ ግንድ አግኝቼ እሱን በመደገፍ ጥቂት እየረዳኝ አንድ ጠረፍ ደርሼ ለመውጣት በቃሁ። ከወጣሁም በኋላ የምሄድበት ቦታ ቸግሮኝ መንገድ እየፈለግሁ ስሄድ ጊዜው መሽቶብኝ ጨለማ ሆኖ ስጨነቅ እሳት በሩቅ አይቼ በብዙ ችግር እየተንገላታሁ መጥቼ እዚህ ብደርስ ደግሞ ገና መከራዬ አላለቀ ኖሮ እነዚህ ወንድሞቼ ሌባ መስያቸው እየደደቡ ይዘው አሰሩኝ፤ ነገሬን ሁሉ ለመናገር ብፈልግ የሚሰማኝ አጣሁ ብሎ አስታወቀው።

ባነጋገሩ ሁሉ ጨዋ ሰው መሆኑን ነጋዴው ስለተረዳው፤ የነገረውም ነገር እውነት መስሎ ስለ ታየው በጣም አዝኖለት እነሱም ባያውቁ ነው በሌት ባሁን ሰዓት አለመንገዱ ስትመታ ስላገኙህ ሌባ መስለሃቸው ነው ለሁሉም ነገር ችግርህን ነገ ሁሉንም ትነግረኛለህ ብሎ እስራቱን አስፈትቶ ታማኙን የጫኞቹን አለቃ ጠርቶ ልስብ ሰጥተህ ራቱንም አብልተህ በደኅና አሳድረውና ጡዋት እኔ ዘንድ ታመጣዋለህ ብሎ አገጣጥሞት ነጋዴው ወደ ድንኳኑ ተመልሶ ሄደ።

በዚያን ጊዜም ነጋዴው ጌታ ይኸንን ሰው በደኅና አነጋገር አነጋግሮ ሲቀበለው ካዩትና ሰውዬውም በርጋታ ሲናገር ከሰሙት ጕረደማኖች አንዳንዶቹ አሳባቸው ያን ጊዜውኑ ተለውጦ ሌባ ሳይሆን አደጋ ያገኘው ሰው በመሆኑ በማጕላላታቸው ተጸጽተው በጣም አዘኑለት። አንዳንዶቹ ግን ምንም ሌባ አለመሆኑን ቢያውቁት ባደረጉት ነገር ሕሊናቸው ያልወቀሳቸው ግድየለሾች ነበሩ።

በዚያን ጊዜም ይኸን መከራ ያገኘውን ሰው ነገሩን በጣም ያሳመነለት አነጋገሩ ሁሉ ያለ ማዛነፍ አጥርቶ ባማርኛ በመናገሩ ነበር። በዚያም አገር በጃውሳነትና በሌብነት የሚጠረጠሩ አንዳንድ ያገሩ ሰዎች ቢኖሩም ከጋልኛ አነጋገር በቀር አማርኛ ደኅና አድርገው አጥርተው ስለማያውቁ አንዱም ምክንያት ሆኖ የረዳው ይኸው ነው።

ያንንም ሰው ነጋዴው አደራ ብሎ ያገጣጠመው የጕረደማኖቹ አለቃ ከድንኳኑ ወስዶ የሚለብሰው ልብስ ሰጥጦ ብርድ በጣም ገብቶት ይንቀጠቀጥ ነበርና እሳት አስነድዶለት እንዲሞቀው አድርጎ የሚበላውና የሚጠጣውም ሰጥቶ ደኅና አድርጎ አሳደረው።

ይኸውም መከራ ያንገላታው ሰው ምንም ገሚሱን ሌሊት አርፎም ቢያድር ያ ውሃ ያጕላላው ከወጣም ወዲያ በዚያ በጭለማ ሲወድቅ ሲነሣ ሲዳክር ያመሸበት፤ ከሰፈርም ሲደርስ ጕረደማኖች የደበደቡት አካላቱ ሁሉ አብጦና ተላልጦ ብርዱም በሰውነቱ ጠልቆ ገብቶ ኖሮ በማግስቱ ጡዋት በጠና ታመመ። ያም ባልደረባ የሆነው የጫኞቹ አለቃ መታመሙን ሂዶ ለነጋዴው ጌታው ነገረው። ነጋዴውም ለዚሁ ለታመመው ሰው እንደሚቻለው መጠን መልካም ነገር የሚያደርግለትን አኳኋን አሰበ፤ አስቦም ያገኘ ይህ ክርስቲያን ነጋዴ፤ ሰው ካለበት መንደር ድረስ በበቅሎ አስቀምጦ ይዞት ሂዶ ለመደሩ ሹም ወይም ሌላ የታመነ ሰው ቢያገኝ ገንዘብ ጨምሮ ሰጥቶ እስኪድን ድረስ እንዲያስታምመው አደራ ብሎ እዚያ እንዲተወውና እንዲሄድ ነበር። ይኸንኑም አሳቡን ለመፈጸም ጭነቱ ሁሉ ተሰናድቶ ጕዞው ሲጀመር በከብት አስቀምጦ ይዞት ለመሄድ ተነሣ፤ ሰውነቱ እንደ ደከመ አይቶት ነበርና ነገርም በመጠየቅ ሊያስቸግረው አልፈቀደም፤ መንገዱንም ሲጓዝ ከበቅሎ እንዳይወድቅ የሚደግፉትና የሚጠብቁት ሁለት ጕረደማኖች ደጋፊ አድርጎለት ነበር።

እስከ ስድስት ሰዓትም ተጕዘው ወዳንዲት የመንደር ከተማ እንደ ደረሱ ሰፈር አደረጉ። ከዚሁም ሰፈር በሽተኛውን የታመነ ሰው ፈልጎ እሱ ዘንድ ለመተው ሲል ወዲያውም በማግስቱ የእሑድ ሰንበት ነበርና አንድ ቀን ውሎ አደረገ። ከዚያው ከመንደ መካከል አንዲት ቤተ ክርስቲያን ነበረችና ከሰፈሩ አድሮ ጡዋት ቅዳሴ ለማስቀደስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዶ

ሳለ የቤተ ክርስቲያኑን አለቃ ስላገኘ ምናልባት እሺ ቢሉኝ እነዚህ ሰው ዘንድ መተው የሚሻል ይመስለኛል ብሎ አሰበ፤ ከቅዳሴ ውጭ ነጋዴው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሹም ዘንድ ሂዶ ለብቻ የምነግርዎ ጥቂት ጉዳይ ነበረኝ ብሎ አላስታወቃቸው ሹሙም ያን ጊዜውኑ ተነሥተው ወዳንድ ገለልተኛ ቦታ አብረው ሂደው ተቀመጡ። ነጋዴውም እባክዎ አንድ ሰው ነበረኝ ታሞብኝ በጣም ስለ ተቸገርሁ ለመንገዴም ስላወከኝና የምተውበት ቦታ ስላጣሁ በዚህ አገር ሰው አላውቅምና የታመነ ሰው አመልክትውኝ የሚታመምበትንም ገንዘብ ጨምሬ ሰጥቼ ለመሄድ ስላሰብሁ የሚያስታምመው ሰው እንደሚያመለክቱኝ ነው ብሎ ስለ ነገራቸው የቤተ ክርስቲያኑም አለቃ ጥቂት እያሰብ ከቈዩ በኋላ እኔ አስታምመዋለሁ እኔ ዘንድ መተው ትችላለህ አሉ። ነጋዴውም ደስ ብሎት ሂዶ ያንን የታመመ አቶ በላይ ካሣን ይዞ ሂዶ በርከት ያለ የመታከሚያ ገንዘብ ላስታማሚው ሰጥቶ አስረክቦ እንግዲህ በሁሉም ነገር አድራዎን ትርፍ ገንዘብም ቢያወጡ ከጥቂት ወራቶች በኋላ እመለሳለሁና ያን ጊዜ እከፍላለሁ ብሎ ነጋዴው መንገዱን ቀጠለ።

በሽተኛው አቶ በላይ ካሣም ብርዱ በሰውነቱ ውስጥ ስለ ገባና ያገኘውም መከራ ሁሉ በጣም ስለ ጎዳው እያሳለው ከዚያው ከቤተ ክርስቲያኑ አለቃ ቤት ብዙ ቀን ታሞ ተኝቶ ሰነበተ። የቤቱም ጌታ አስታማሚው በሚቻለው ሁሉ ደኅና አድርጎ አስታመመው፤ በተቀበለውም ገንዘብ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በክርስቲያንነት ወንድምነቱም በጣም አስቦ ያስታምመው ይረዳው ነበር። ከሦስት ወር በኋላም በሽተኛው ሕመሙ እየተሻለው ማገገም ጀመረ። ጥቂት ቀኖችም ቈይቶ ሕመሙ ፈጽሞ እንደ ተሻለው ሚስትና ልጆቹን ማሰብ የት ደርሰው ይሆን ምንስ አግኝቷቸው ይሆን በማለት እነሱ የሆኑትን ነገር ያሉበትን አገር ለማወቅ ዋና አሳቡ ሆነ። በዚያውም ሰሞን አንድ ቀን አስታመው ያዳኑትን አለቃ ሥዩምን ባደረጉለት ርዳታ ሁሉ በጣም አመስግኖ ውለታዎን እግዚአብሔር ይመልስልዎ እንጂ፤ እኔ የምከፍልዎ ነገር የለኝም እንግዲህ ሚስትና ልጆች ያሉኝ ሰው ነኝና ይህ ሁሉ አደጋ ያገኘኝ እንዲያውም ካልሆነ ስፍራ ትቻቸው ስለ ሆነ ምናልባት ባገኛቸው እነሱን ሂጄ ለመፈለግ እፈቅዳለሁ

አላቸው። አለቃ ሥዩምም መልካም ነው ሂደህ ፈልጋቸው ብለው ሥንቅ እንዲሰናዳለት አደረጉ፤ በዚያን ጊዜም አቶ በላይ ካሣ ደግሞ ሌላ ነገር አሰበ፤ ያንን መልከማ ሥራ የሠራለትን እዚያ ድረስ አምጥቶ ገንዘቡን ሰጥቶ እንዲያስታምሙት አድርጎ የሄደውን ነጋዴ ስሙን አያውቀውም ነበርና አለቃ ሥዩምን የቤቱን ጌታ ቢጠይቅ ያም ያገኘው ያንለት ብቻ ለዚሁ ጉዳይ ስለ ሆነ ያንጊዜም እንኳን ስሙን ሰምቶት ቢያውቀውም ዘንግቶትና ረስቶት ነበርና ስሙን ባለማግኘቱ ጥቂት አዘነ። ሊያውቅም የፈለገበት ምክንያት ላደረገለት ወሮታ ምንም እንኳን የሚመልስለት ገንዘብ ባይኖረው ፈልጎ ባገኘው ጊዜ ባደረግህልኝ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ብድሩን ይክፈልህ ብሎ ማለትን እንደ ትልቅ ነገር አስቦለት ይህንኑ እንዲነግረው ነበር። ነጋዴውም ቢፈቅድለትስ ሌላ ገንዘብ ባይኖረው ባገልግሎት ውለታን ለመመለስ ይፈልግ ነበር። ነገር ግን መልካም ሰዎች የሚሠሩትን ደግ ሥራ ያለው ያገልግሎት ብድር መመለስ እንደማይሹ ያውቅ ነበርና፤ እንዲያው ብቻ ምስጋናውን ላምቅረብ ነበር የፈለገው። በዚሁ ስሙን ባለማወቁ ለጊዜው ቢቸገርም የሸዋ ነጋዴ መሆኑን ተረድቸዋለሁ የሚስቴንና የልጆቼን መቸረሻ ነገር ካወቅሁ በኋላ እዚያው እንጦጦ ከተማ ደረስሁ እነጋዴዎች ሰፈር ሂጄ በመልኩ እፈልገዋለሁ በማለት ነገሩን ወስኖ ተመልካሙ አስታማሚው ካለቃ ሥዩም ተሰነባብቶ መንገዱን ለመሄድ ተነሣ።

አቶ በላይ ካሣም ለመሄድ ባሰበ ጊዜ የቤተ ሰቦቹን ወሬ ለመጠየቅ እንዲመቸው በደጀን በኩል ያባይ መልካ መሻገሪያ ወዳለው የሰላሌ አውራጃ ግዛት ጃርሶ ከሚባለው ወረዳ አገር ጎሐ ጽዮን ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ጥቂት ቀን ውሎ አድሮ የሚያገኛቸውን መንገደኞች ለመጠየቅ ነበር፤ ቤተ ሰቦቹ ወደ ሸዋ የሚያውቁት ሰው ስለሌላቸው ምን አልባት ወዳገራቸው ተምልሰው ይሆን በማለትም ይተረጥር ነበር። እዚያው ጎሐ ጽዮን ሂዶ እንደ ደረሰ አቶ በላይ በልጅነቱ ያገራችንን ትምህርት ተምሮ ቅኔም መቀኘት ስለሚያውቅ ስምንት ቀን ያህል ጎሐ ጽዮን እመቤታችን ማርያም ቤተ ክርስቲያን እያገለገለ አንድ መቃብር ቤት ሰንብቶ በዚያውም ሳምንት ውስጥ ብዙ ጊዜ ወዳውራው ጐዳና መንገድ እየሄደ ከጐጃም ወደ ሸዋ የሚሄዱትን መንገደኞች ሲያገኝ ስለ እሱና ስለ ቤተ ሰቦቹ በጐጃም

የሚወራውን ወሬ ይጠይቅ ነበር። ይኸንኑም ወሬ ሲጠይቅ እሱ መሆኑን ድንገት አስቀድሞ የሚያውቁት ሰዎች እንዳያውቁት ጢሙን ላጭቶ መልኩን ለዋውጦ ዘመዴ ነች እያለ ነበር፤ አግኝቶም የሚጠይቃቸው አንዳንድ መንገደኞች የሚበዙት ያስታውቁት ገባሩ በርስቱ በጉልቱ ላይ ቢሾምበት አገር ጥሎ ቁርበት ጠቅሎ ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ጠፍቶ ሄዶ ይባላል የሄደበትንና የደረሰበትን ቦታ የሚያውቅ የለም። አንዳንድ ሰዎች ግን ምናልባት ወደ ሸዋ ሄዶ ይሆናል የሚሉ አሉ ሌላ ምንም ወሬ ስለ እሱና ስለ ቤተ ሰቡ የምናውቀው የለም እያሉ ይነግሩት ነበር። እሱም ያገኘውን ሰው ሁሉ ወሬ ከጠያየቀ በኋላ ወደዚያው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተመልሶ ብቻውን በሆነበት ጊዜያት ጠሊቅ የሆነ ሐዘን ለሰውነቱ እየተሰማው የቅኔ እንጉርጉሮውን በዜማ የሚያደርገው ብዙ ጊዜ እየመላለሰ ከሌሎቹ ይልቅ ዝማሬ ዘመስቀል የሚባለውን ቀጥሎ የተጻፈውን ነበር።

መዓልተ በጽሙና ወሌሊተ በህሉና፤

አንሰ ስእንኩ ለዛቲ ዓለም መጠና፤

ንብረታኒ ሙስና ወብዙኅ ሐዘና፤

አንሰ ስእንኩ ለዛቲ ዓለም መጠና፤

ዕፀ መስቀሉ ለወልድ ለነፍስየ ፀወና አንሰ

ስእንኩ ለዛቲ ዓለም መጠና፤

ብፁዕ ውእቱ ዘመነና ይበልዕ ኅብስተ መና፤

ወታሰትዮ ቤተ ክርስቲያን እም ወይና፤

አቶ በላይ በዚያው ሳምንት ውስጥ ደግሞም የሚስቱ ወገን ዘመዶቹ የሆኑ መንገደኞች አግኝቶ እነሱ ሳያውቁት እሱ ዐውቋቸው የቤተ ሰቦቹን ወሬ ቢጠይቅ እንደዚያው ሁሉ በፊት እንደ ሰማው ጠፍተው መሄዳቸውን እንጂ፤ ሌላ የሚያውቁት ወሬ አለመኖሩን፤ የሚስቱም እናትና አባት በዚሁ ነገር ሲጨነቁ መሰንበታቸውን ብቻ ስለ አስታወቁት ወደ ጐጃም አለመመለሳቸውን ቍርጡን ነገር ያወቀው ያህል ላሳቡ ተረዳው።

ከዚያው በኋላ ሌላ ሐሳብ ደግሞ በሰውነቱ ይወጣ ይወርድ ጀመረ። ምናልባት ሚስቴ እኔን ውሃ ሲወስደኝ አይታ እሷዋ እወንዙ ውስጥ ገብታ ሞታ ልጆቼን አውሬ በልቷቸው ይሆን እያለ ተቸግሮ ጥቂት ከቈየ በኋላ የእሱን ወይም የእነሱን ወሬ የሚያገኝበት ብልኀቱ ጠፍቶት ማዘን ተሰፋም መቍረጥ ጀመረ።

ብዙ ጊዜም የሰውነቱን መታወክና መበሳጨት የአእምሮ አሳቡን መቅበዝበዝ የሚያስታግሥለት የክርስቲያንነት የሃይማኖት ተስፋው ብቻ ነበር። እዚያም ኀሐ ጽዮን አንድ ሳምንት ከቈየ በኋላ ወደ ሸዋ ዋና ከተማ ወደ እንጦጦ ሂዶ ያንን በጎ ሥራ የሠራለትን ነጋዴ ለመፈለግና ወደፊትም የሚኖርበትን የትዳሩን ነገር እዚያ ከደረሰ በኋላ ለመወሰን አስቦ ወደዚያው ጕዞውን ያዘ።

እንጦጦ ከተማ በደኅና እንደ ደረሰ የሚያውቃቸውን ከዘመድም ሆነ ከወዳጅ አንድም አላገኘም፤ በዚያ ዘመንም እንደሱ ላለ መንገደኛ ሰው ሁሉ የእንግዳ ቦታ ወይም ሆቴል ባለመኖሩ ገንዘብ እንኳን ቢኖረው የሚያርፍበት ቦታ ለማግኘት ብዙ ችግር ነበረበት። እሱ ግን በዚያን ጊዜ ወደ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ሂዶ አንድ ባዶ የመቃብር ቤት ስላገኘ ከዚያ ገብቶ ዐርፎ እቤተ ክርስቲያንም ጥቂት ጥቂት ያገልግሎት ሥራውን እየሠራ ያንን ነጋዴ መፈለግና የሚይዘውንም ሥራ መመርመር ሲጀምር ነጋዴውን በየገበያው ቦታና በነጋዴዎችም ሰፈር እየሄደ እያየ እየተመለከተ ሰሞኑን ቢፈልግ ሳያገኘው ቀረ።

ስለ ትዳሩ ግን አስቦ የወሰነውና ያገኘውን ወደ ሐረርጌ ሄዶ በወታደርነት ሥራ አገልግሎቱን ለማድረግና በዚያው ትዳሩን ለመያዝ ነበር። ይኸንኑም ያሰበበት ምክንያት በዚያ ወራት ሐረርጌን አጼ ዮሐንስ በንግግር አስቀድሞ ቱርኮችን ስላስለቀቋቸው አጼ ምኒልክ ራሳቸው ከሸዋ የጦር ሠራዊታቸው ጋር አገሩን ለመያዝ ዘምተው ሄደው ሳለ ቱርኮች ሲሄዱ ከዚያው የነበረው ያገሩ ባላባት የሐረርጌው አሚር ጨለንቆ ከሚባለው አገር ድረስ ሂዶ ስለ ተዋጋቸው እሱን ድል አድርገው አሸንፈው ሽረው ባላምባራስ መኰንንን ደጃዝማች ብለው ላገሩ ገዥ እንዲሆኑ ሾመው ከሠራዊታቸው ከፍለው ሰጥተው በደጃዝማች መኰንን ውስጥ

የሚተዳደሩ ብዙ መኳንንትና ወታደሮች ትተው አጼ ምኒልክ ተመልሰው ነበርና እዚያ የቀረው ጦር የማይበቃ በመሆኑ ሰው ይፈለጋል ደኅና ትዳርም ማግኘት ይችላል እየተባለ ስለሚወራና በዚያን ጊዜም አቶ በላይ ይኸንን ሰምቶ ስለ ነበረ፤ ወደዚያው ለመሄድ አስቦ የወሰነው ስለዚሁ ነበር።

ከጥቂጥ ሳምንቶችም በኋላ ወደዚያው የሚሄዱ መንገደኞች ፈልጎና ተስማምቶ ጓደኛ ሆኖ ወደ ሐረር ተጓዘ። ሐረርጌም እንደ ደረሰ በዚያን ጊዜ ከሸዋ የሚመጣ ሰው ሁሉ በጣም ይፈለግ ስለ ነበረና እንደ ተገኘም ባልደረባ ተደርጎለት የወር ቀለብና ያመት ደመወዝ እንደ ማዕርጉና እንደ ጓዙ መጠን የሚቀበለው ስለ ነበረ፤ አቶ በላይም ያጋፋሪ ባልደረባ ሆኖ የጨዋ ቀለብና ደመወዝ አግኝቶ ቤትም ተሰጥቶት ለመቀመጥ ቻለ።

ከጥቂት ወራቶችም በኋላ አቶ በላይ ባገልግሎት ሥራው ባለቆቹ ዘንድ የታመነና የተመሰገነ ሆኖ አንድ ዓመት ከቈየ በኋላ፤ በደጃዝማች መኰንን ዘንድ መታወቅ ጀመረ።

ደጃዝማች መኰንን በሰንበትና በየሌላዎቹም በዓላቶች ቀን ከቤተ ክርስቲያን ማልደው በሚሄዱበት ጊዜ ሁሉ አቶ በላይ ካሣን በቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ ስለሚያገኙት በሌላውም ጊዜ ደጅ ጥናቱንና ሥራውን በመጠንቀቅ ሲሠራ ስለሚያዩት አንዳንድ ጊዜ አቅርበው እያነጋገሩት ወደውት ትዳሩም ጥቂት በጥቂት ተሻሽሎለት ነበር።

በዚያም ወራት በያንዳንዱ ወገን፥ አገሩ በጣም ደኅና ሆኖ አልተረጋጋም ነበርና በግሪ ወረዳ በኩል የቆላው ሱማሌ ከደገኛው ባላገር ጋራ ተስማምቶ በዚያ ክፍል የነበሩን የደጃዝማች መኰንንን መኳንንቶችና ወታደሮች ለመውጋት ሁከት በተነሣሣበት ጊዜያት አቶ በላይ ካለቆቹ ጋራ ለርዳታ ታዝዞ ሄዶ ትልቅ የጀግንነት ጀብዱና ሞያ ስለ ሠራ ትንሽ የሹመት ማዕርግ አግኝቶ ተከብሮ ተቀምጦ ሳለ ከደጃዝማች መኰንንም የመቅረብና የመውደድ ፍቅር በማግኘቱ አንዳንድ ሹማምንቶች አብዝተው የሚቀኑበት ነበሩ። እሱ ግን በመልካምና በቅንነት ዐመሉ ያገልግሎቱን ሥራ ሳያቋርጥ ክፉም ለሚሠሩበት መልካም እየመለሰ በመበርታቱ ሁሉም ሊያሸንፉት አልቻሉም። እንዲያውም የነሱ ተንኰልና ክፋት በሱ መልካም ሥራ

ይገለጥባቸው ጀመር። ይልቁንም እሱ ሹመት እየጨመረ የታወቀ መኳንንት ሆኖ ከፍ ከፍ እያለ ስለ ሄደ፤ ከጥቂቶች ዓመታት በኋላ ያጋፋሪነቱን ዋና ሹመት ፊታውራሪ ተብሎ ለሱ ተሰጥቶ ሰውን በማግባትና በማውጣት በማስተናበር ደኅና የሚሠራ ሆነ።

በዚያው ሰሞን አንድ ነጋዴ ከሸዋ ወደ ሐረርጌ የሚወደደውን ዕቃ ጠይቆ አሰናድቶ ለመነገድ በብዙ አጋሰስ አስጭኖ ይዞ ሲወርድ በደኅና ሲጓዝ ሰንብቶ ደደር ከሚባለው ወረዳ አገር ጫካ ደን ውስጥ ሲደርስ ወንበዴዎች ዕቃውንና ከብቱን ዘርፈውት እሱና ሰዎቹም በመከራ አምልጠው ሄደው ለወረዳው ሹም ያገኘውን አደጋ (የሄደበትን) የተዘረፈውን ከብትና ዕቃ በጽሕፈት አድርጎ ካስታወቀ በኋላ፤ ከዚያው ጥቂት ቀን ቈይቶ ምንም ሳይደረግለት ስለ ቀረ፤ ለዋናዎቹ ዳኞች ለማስታወቅ ሰዎቹን ይዞ ወደ ሐረር ሄደ። ሐረርጌም እንደ ደረሰ ዳኞቹ ወዳሉበት ዐደባባይ ሲሄድ ድንገት ፍታውራሪ በላይ ስለ አየው እንግዳ ሰው መሆኑን ተመልክቶ እሱ ዘንድ አስተርቶ አንተ ሰው ከወዴት አገር ነው የመጣኸው ሥራህስ ምንድነው ብሎ ስለ ጠየቀው ከሸዋ ነው የመጣሁት ሥራዬም ንግድ ነው። የንግድ ዕቃ አስጭኜ ይዤ ስመጣ ደደር ከሚባለው አገር ስደርስ ጃውሶች ከብቴንና ዕቃዬን ሁሉ ስለ ዘረፉና ስለ ወሰዱብኝ ለወረዳውም ሹም ሄጄ ባስታውቅ ምንም ያደረገልኝ ነገር ስለሌለ ለበላይ ዳኞች ለማስታወቅ ነው አሁን ወደዚህ የመጣሁት አለው።

አቶ በላይ በጣም ትኩር እያደረገ ሲያየው ቈይቶ ነበርና ነጋዴ መሆኑን ካወቀው በኋላ ጥቂት ጥቂት ካባይ ውሃ ወጥቶ መከራ ባገኘው ጊዜ በጎ ሥራ ያደረገለትን ነጋዴ መሰለው፤ ጊዜው ዘመኑ በዝቶ ወደ ዐሥራ ሦስቱ ዓመት ሆኖት ነበርና እሱ ይሆን ወይስ አይደለም ይሆን በማለት ተጠራጠረ። ያን ጊዜም ያየው እንደ ታመመ ሁለት ቀን ብቻ ነበርና ለማረጋገጥ አስቸገረው። ጥቂት እያሰበም ቈይቶ በማናቸውም አኳኋን ማንም ሰው ቢሆን እንደዚህ ያለ አደጋ ያገኘውን ሰው መርዳት የሚገባ ነውና ሌላውን ነገር በኋላ እጠይቀዋለሁ ብሎ ፊታውራሪ በላይ ወደ ደደር ወረዳ ሹሞች ነጋዴው ያመለከተውን ጽፎ የተዘረፈውን ከብቱንና የንግድ ዕቃውን ጃውሶችንም ጭምር እስከ ዐሥር ቀን ድረስ አሲይዘው እንዲነሱ

በዚህ በተወሰነው ቀን ውስጥ ሳይልኩ የቀሩ እንደ ሆነ እነሱው ያገሩ ሹማምንቶች ለጥፋቱ ሁሉ ኃላፊ መሆናቸውን አስረድቶ ጥብቅ ትእዛዝ ጽፎ ላከ። ወዲያውም እዚህ አደባባይ ብዙ ነገር ከመጠየቅ ወደ ቤቴ ወስጄ ጋብዤ ብጠይቀው ይሻላል ብሎ አሽከሮቹ አንዱን ጠርቶ ለዚህ ነጋዴ ባልደረባ ሁነው ኋላም ወደ ቢታችን በምንሄድበት ጊዜ ከኛው እንዳይለይ አብሮን ወደ ቤት እንዲሄድ ብሎ አገጣጥሞት ወደ ሥራው ገባ። ሥራውንም ጨርሶ ወደ ቤቱ እንደ ሄደ፤ ነጋዴውም አብሮት ሂዶ ነበርና የተሰጠው ባልደረባ እዚያ መኖሩን ለጌታው አስታወቀ። ፊታውራሪ በላይም የምሳ ጊዜ እንደ ደረሰ ጥሩት ብሎ አብረው ምሳቸውን እየበሉ ፊታውራሪ በላይ አንዳንድ ነገር ይጠይቀው ጀመር፤ ወንድሜ ሆይ የትውልድ አገርህ የት ነው፤ ስምህስ ማን ይባላል። ነጋዴው የትውልድ አገሬ ሽዋ በቡልጋ ወረዳ ውስጥ ነው ስሜም ገብረ መድኅን ይባላ ጥ... የንግድ ሥራህንስ ጀመርህ ስንት ዓመት ይሆንሃል የምትነግደውስ ወዴት ወዴት አገር ኖሮዋል ፡

መ.... የንግድ ሥራዬን ጀመርሁ ወደ ዐሥራ አምስት ዓመት ይሆነኛል፤ በፊትም የምነግድባቸው የነበሩት አገሮች ከሽዋ ወደ ጐጃም ከጐጃምም ወደ ሽዋ በግንደ በረት በኩል እየተመላለስኩ፤ ማር፤ ቅቤ፤ ጨርቃ ጨርቅ እየወሰድኩ በያገራቸው ላይ የሚወደደውንና የሚረከሰውን ዕቃ እየተመለከትሁ ከሚረክስበት ወደሚወደድበት እየወሰድኩ ስሥራ ቈይቼ ሳለሁ በዚያ በጐጃም በኩል በምሠራው ንግድ ትልቅ ትርፍ የማላገኝበት ስለ ሆነ፤ ወደ ወሎ በኩል በባቲ ወገን አዛውሬ በቆዳና በሌላም በያንዳንድ ሸቀጥ መነገድ ከያዝሁ ወደ ስድስቱ ዓመት ሆኖኛል። አሁን ግን ሐረርጌ አንዳንድ ነገር በጣም የሚፈልግ አለ ስላሉኝ ያንኑ ጠይቄ አሰናድቼ ይዤ ስመጣ ነው ይኸ አደጋ ያገኘኝ አለው።

ፊታውራሪ በላይም ከስድስት ዓመት በፊት ከሽዋ ወደ ጐጃም በግንደ በረት በኩል እየተመላለስኩ እነግድ ነበር ስላለው፤ ያ ወሮታ የዋለልኝ ይኸው ሳይሆን አይቀርም በማለት በጣም ስለ ጠረጠረ ለማረጋገጥ ፈልጎ ጥያቄውን ቀጠለ።

ጥ..... አሁን ወደ ዐሥራ ሦስቱ ዓመት ይሆናል እኔም እዚያው ግንደ በረት ነበርኩና ከቤተ ክርስቲያን አንድ ቀን እሑድ አንተኑ የሚመስል ሰው አይቼ ነበር፤ ምናልባት አንተ ትሆን ይሆን?

መ... እሆን ይሆናል በዚያን ጊዜ አንድ የታመመ ሰው ነበረኝና በሕመሙ ምክንያት ለመንገዴ ስለ ተቸገርኩ እሱን የምተውበት ቦታ ስፈልግ ወደዚያው ሄጄ ነበር ወዲያውም ቀኑ ዕለተ ሰንበት ነበርና ቅዳሴ ለማስቀደስ ቈይቼ ሳለሁ ያን ጊዜ አይተውኝ ይሆናል አለው።

ጥ... በዚያን ጊዜ የነበሩትን የቤተ ክርስቲያን አለቃ ታውቃቸዋለህን?

መ.... አዎን ዐውቃቸዋለሁ አለቃ ሥዩም የሚባሉ ነበሩ፤ በሽተኛዬንም ትቼ የሄድኩት እሳቸው ዘንድ ነበር።

ጥ.... ታሞ ከዚያ የተውከው ሰውስ ስሙ ማን ይባላል፤ ከዚያስ ወዲህ በሽትውን ድኖ አግኝተውኸው ኖሯልን?

መ.... ካንድ መንፈቅ በኋላ ለዚያው ለንግድ ሥራዬ ወደ ጐጃም ስሄድ ግንደ በረት እንደ ደረስኩ ወደ አለቃ ሥዩም ዘንድ ሄጄ ጠይቄያቸው ነበር፤ እሳቸውም በሽታውን ድኖ ዳዞች ሚስትና ልጆች አሉኝ ብሎ ከሄደ ብዙ ቀን ሆኖታል አሉኝ። እኔም ድንገት ነበርና ያገኘሁት ወዲያው ስለ ታመመ ነው ከዚያ የተውሁት፤ ስሙን የማውቀው አልነበረ፤ ከእኔም ጋራ ብዙ ቀን የቈየ ሰው አይደለም አለው።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ነጋዴ ገብረ መድኅን ይኸ የሚጠይቀው ሰው እሱ ነው ብሎ ምንም የጠረጠርውና ያሰበው አልነበረም፤ ፊታውራሪ በላይ ግን በጠየቀው ጥያቄና በመለሰለትም መልስ አረጋግጦ እሱ መሆኑን ስለ ተረዳውና ስላወቀው ተነሥቶ ደጉና መልካሙ ሰው ገንዘብህን ሁሉ ሰጥተህ ለአለቃ ሥዩም ታሞ እንዲድን ያደረግኸው ሰውህ እኔው ነኝ ብሎ የደስታ ዕንባ እያነቀው ቀርቦ ጉንጬን ሳመው።

ነጋዴው ገብረ መድኅንም ደንግጦ ለጊዜው እውነት አልመሰለውም ነበር፤ ደግሞም ለእግዚአብሔር ብሎ በክርስቲያንነት ስሜቱ የሠራው እንዲታወቅና እንዲወራለት አይሻም ነበር።

ያን ጊዜም ፊታውራሪ በላይ ካሣ የሚያርፍበትን ቦታ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ለወዳጅ የሚገባውን አንድ ነገር ሳይጐድል አሰናድቶ ነጋዴ ገብረ መድኅንን ከነሰዎቹ እንግድነቱን ተቀብለው፤ እሱንም ከብዙ ዘመን በኋላ ስላገኘው እግዚአብሔርን አመስግኖ እጅግ ደስ አለው።

ጥቂት ቀኖችም ውሉ አድሮ የደደር ሹም የነጋዴውን ከብትና ዕቃ የዘረፉትን ጃውሶች ሁሉ ከነዕቃቸው አሲዞ ልኮ አንድም ነገር ሳይቀር ለነጋዴ ገብረ መድኅን ገንዘቡ ደረሰው።

በዚያን ጊዜም ፊታውራሪ በላይ ካሣ የዚህን ነጋዴ መልካም ሰውነት አስታውቆ ከደጃች መኰንን ጋራ ለማገናኘትና ለማስተዋወቅ ስለ ፈለገ አንድ ቀን ወስዶ ይህን ሰው አስቀድሞ የማውቀው እውነተኛ ክርስቲያን መልካም ሰው ነው ብሎ አመልክቶ አገናኘውና አስተዋወቀው።

ደጃች መኰንንም እንደዚህ ያለውን ቅን ክርስቲያን እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በጣም ይወዱ ነበርና የነጋዴውን ፈቃድ ቢሆን እዚያው እርሳቸው ዘንድ ሐረርጌ ቀርቶ አንድ ሥራ ለማስያዝ አስበው እንዲጠይቀው ለፊታውራሪ በላይ ነግረውት ነበር።

ፊታውራሪ በላይም እንደሱ ያለ ባልንጀራ ወዳጅ ለመላ ሕይወቱና ዕድሜው ለማግኘት ይመኝ ነበርና ያንኑም ምክንያት ስላገኘ ሰሞኑን የደጃዝማች መኰንንን መልካምነት አበርትቶ እያስታወቀ ነጋዴ ገብረ መድኅን እዚያው ቀርቶ የደጃዝማች አሽከር ሆኖ እንዲቀመጥ አጠንክሮ ለመነው። እርሱም አስቀድሞ ያሰበው ፈቃዱ ኖሮ ጥያቄውን በደስታ ተቀበለው።

ይኸንኑም ፊ. በላይ ለደጃዝማች መኰንን አስታውቆ ነጋዴ ገብረ መድኅንን በነጋድራሶቹ ወገን የክፍል ሥራ እንዲይዝ ባልደረባ ተሰጥቶት የጨዋ ማደሪያም እንደሚገባው ተደርጎለት እንዲቀመጥ አደረገው።

ከጥቂቶች ዓመታቶችም በኋላ ነጋዴ ገብረ መድኅን ሥራውን በታላቅ መታመንና ጥንቃቄም ሠሪና ፈጻሚ በመሆኑ የሐረር ዋናው የነጋድራስነት ሹመት ተሰጥቶት ደጃዝማች መኰንንንም በአገልግሎቱ ደስ የሚያሰኝ ሆኖ

ተቀመጠ። ከፊ በላይ ካሣም ጋራ ፍቅራቸውና ወዳጅነታቸው፤ መተማመናቸውና ባልንጀርነታቸው እያደረ እየበረታ አብረው ኖሩ።

በአጼ ምኒልክና በኢጣሊያኖች መካከል ያለመግባባት የተሠራው የውጫሌ ውል ሲፈርስ ታላቅ ጠብ ተነስቶ ኢጣሊያኖች በትግሬ በኩል ወሰን አልፈው አገር መውረር ሲጀምሩ አጼ ምኒልክም በኢትዮጵያ ላለ ሕዝብና ሠራዊታቸው የክተት ዘመቻ ዐዋጅ አስነግረው ደጃዝማች መኰንንን ራስ ብለው የራስነት ማዕርግ ሰጥተው ሾመው ከራስ ሚካኤል ከወሎው ገዥ ጋራ ጠቅላይ አዛዥ የቶር አበጋዝ አድርገው አሽንጌ ድረስ ዘልቆ የመጣውን የኢጣሊያንን ጦር ቀድመው ሄደው እንዲዋጉ አጼ ምኒልክ አዘዋቸው ሲሄዱ ከሐረር ብዙ ሹማምንትና ወታደር ከሸዋ ወገንም እንዲሁ ታዞ አብሯቸው የሚሄድ ብዙ መኳንንትና ብዙም ሠራዊት ተጨምሮላቸው ከሳቸው ጋር ቀድሞ አብሮ ሱዳዝ ፊ ገበየሁ የሚባለው ያጼ ምኒልክ ያንዱ ክፍል የጦር አለቃ በራስ መኰንን ግንባር ላለ የጦር ሠራዊት መሪ ሆኖ ሌላውም በከንባታ በጉራጌ ያለ ጦር ከሐረርጌው የጦር ወታደር ጋራ አብሮ ሆኖ ወደ ፊት ወደ ግንባራቸው ወገን ያሉትም የወሎ፤ የየጁ፤ የዋድላ፤ የደላንታ፤ የበጌምድር፤ የላስታ፤ የዋግና የትግሬ ጦር ከራስ ሚካኤል ጋራ አብሮ እንዲዘምት አስቀድሞ ታዘዘ። በስተ ኋላ ደግሞም የመኻል ሰፋሪንና የየዳር አገሩን የጦር ሠራዊት እስከትለው አገር ጠባቂ ሹማምንትና ወታደርም እያዩ በየቦታው በያገሩ ትተው እርሳቸው አጼ ምኒልክ ባለቤታቸውም እቴጌ ጣይቱ ሳይቀሩ ከራስ መኰንንና ከራስ ሚካኤል ጋራ ለቀደመው ጦር እንደ ደጀን ሆነው ተከታትለው ተነሡ።

አጼ ምኒልክም ኰራማሽ ራስ መኰንን ደሴ ፊ ገበየሁ ጐልቦ ላይ በሰፈሩበት ቀን ቦሩ ሜዳ ከሚባለው አገር ላይ በራስ መኰንን የግንባር ጦርና በፊገበየሁ የጀርባ ጦር የችፍራ አለቆች መካከል ትልቅ ጠብ አምባጓሮ ተነሥቶ ነበር። ጠቡም የተነሣበት ምክንያት አንድ ትልቅ መንደር መሳፈሪያ ለመያዝ በመሻማት ሁለት የጭፍራ አለቆች ተገናኝተው በዚያው ተጣልተው ነው። በዚሁ አገር ላይ ያንድ ትልቅ ሹም ሰፊ አጥርና ብዙ ቤቶች በውስጡ ያሉበት ነበር።

አንደኛው በራስ መኰንን የግንባር ሰፋሪ ክፍል ባሻ ጌታነህ የሚባል ከሶዱው ከጉራጌው አገር ዘማች ውስጥ ያንድ ጭፍራ አለቃ የሆነ ያንን ትልቅ መንደር ይዞ ለመስፈር ስለ ፈለገ፤

እንደሱም ደግሞ ከፊታውራሪ ገበየሁ ከሸዋ ጦር ጀርባ የሰፈረው ባሻ ካሣሁን የሚባል አንድ የሻለቃ ያንኑ ቤት ይዞ ለመስፈር ስለ ፈቀደ እኔ ነኝ በፊት የደርስኩ በመባባል ትልቅ ያንባጓሮ ጠብ ተነሥቶ እጅግ ተማረው ጠመንጃ እያጕረሱ ለመታኰስ ደርሰው ድብልቅልቁ የወጣ ጩኸት እየተጮኸ ከነጭፍሮቻቸው ተሳልፈው ሳለ ይኸውም የተጣሉበት ብዙ ቤቶች ያሉበት ባለ ሰፊ አጥር ግቢ የዚያው የቦሩ ሜዳ ቀበሌ ጭቃ ሹም አቶ አልዩ የሚባል ሰው ቤት ነበረ። ባለቤቱም አቶ አልዩ በጭቃ ሹምነቱ አገሩን መጥን (መተያያ) አዝዞ ሠንጋ ጭምር አሰናድቶ ያንኑ ደሴ ወስዶ ለማስረከብ አሲዞ ስለ ሄደ በዚያን ጊዜ በቤቱ አልነበረም። ሚስቱ ግን እዚያው እቤቱ ስለ ነበረች በዘማቾቹ መኻል የተነሣውን ሽብርና ጠብ እግቢዋ አጠገብ ስለ ሰማችና ስላየች በቶሎ እሱዋው ራስዋ ያሉትን አሽከሮች አስከትላ ወጥታ ከሚጣሉበት መኻል ገብታ ምነው ወንድሞቼ በምን ነገር ትጣላላችሁ ዛሬ ጠላት መጣ እየተባለ ያንን ለመቃወም ስትሄዱ አንድ ሆናችሁ ተስማምታችሁ ሥራችሁን በምትሠሩበት ሰዓት ምን ያጣላችኋል ብላ የተጣሉበት በሰፈር መሆኑን አስቀድማ ሰምታ ስላወቀች ለመሳፈሪያም እንደ ሆነ ለሁላችሁም ግቢያችን ይበቃል ለእናንተ ለሹሞቹ አንድ አንድ ቤት እንሰጣችኋለን ለጭፍራችሁም ብዙ ስፍራ ስላለ በዙሪያው እየተጠጋ ይሰፍራል። ለኛም ሌላው ዘማች እየመጣ እንዲያስቸግረን እንደ ዘበኛ ትሆኑናላችሁ ለከብታችሁ ሣር ለናንተም የተገኘውን እኽልና ውሃ እንሰጣችኋለን ላንድና ለሁለት ቀን አዳር ብላችሁ ለሁላችሁም የሚበቃ ቦታ እያለ የሚያጣላችሁ ነገር ያለ አይመስለኝም እያለች በትልቅ የትሕትና ወቀሳ ቃል ስለ ነገረቻቸው ሴትዮዋ ጨዋ የከበረች ሴት መሆንዋን ባነጋገሩዋ ሁሉ ተመልክተው ነገሩዋን በጸጥታ አድምጠው ሰምተው ነበርና ጠባቸውን ፈጽመው ትተው እሺ የነገሩን ሁሉ እውነት ነው፤ እንደ ፈቃድዎ እናደርጋለን ብለው ሁለቱም መልስ ሰጧት። ከዚህ በኋላ ለሹሞቹ የሚያርፉበት አንዳንድ ቤት፤

ለሰዎቻቸውም በዚያው ዙሪያ የሚሰፍሩበት ቦታ አብቃቅታ ሰጥታ የተነሣሣው ጠብ ሁሉ ቀርቶ ሰላም ሆነ።

ወደ ማታም ጊዜያት ባለቤቱ ጌታው አልዩ መታያውን አስረክቦ ወደ ቤቱ እንደ ተመለሰ ተነስቶ የነበረው የነበረውን አንባጓሮና ሚስቱም ገልጋል ጠቡን አብርዳ ለሁሉም ቦታ እንዲያገኙና እንዲሰፍሩ ማድረጉዋን ስለ ሰማ ደስ ብሎት ባለቤቱን በጣም አመሰገናት፤ የራታቸውም ጊዜ ሲደርስ ሁለቱንም እንግዶች ሹሞች አብረው ራታቸውን እንዲበሉ ስለ ፈቀዱ ካረፉበት ልከው አስጠሩዋቸው። መጥተውም ራት ቀርቦ አብረው ሲበሉ ጨዋታ ጀምረው የባሶው ባሻ ካሣሁን አንደኛው እንግዳ ዛሬ እሜቴ መጥተው በርትተው ባይገላግሉን እንዲህ ለሁላችንም የሚበቃ ቦታ ሳይጠፋ በማይጠቅም ነገር ከክፉ ልንዳረስ ነበር፤ እግዚአብሔር እንደ መልአክ እርስዎን ልኮልን ከክፉ ነገር ሁሉ አዳኑን፤ እንኳንስ ሌላውን ሁሉ አድርገውልንና ሲገላግሉ ያስታወቁን የምክር ቃል ከልቤ ውስጥ ገብቶ ብርቱ ተግሣጽ ሆኖኝ ከትልቅ ነገር ቈጥሬዋለሁ። በተደረገልንም ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ አለ። ባለቤቱም ጌታው አልዩ እኔ በሌለሁበት ጊዜ ስለ እናንተ ያደረገችውን ስለ ሰማሁ በጣም ደስ ብሎኛል። ላንድ ቀን የሰፈር አዳር ፊቱንም የሚያጥላችሁ ነገር አልነበረም ብሎዋቸው በራታቸው መኻል እንደዚሁ አንድ አንድ ንግግር እያመጡ ሲጫወቱ ከወደ ጉራጌ አገር የመጣው ሁለተኛው እንግዳ ባሻ ጌታነህ የሚባለው በጣም ዝምታ በማብዛት ብዙ አልተናገረም ነበርና የቤቱዋ ባለቤት ወንድሜ አንተስ ወዴት አገር ኑሮዋል የምትኖረው ከወዴት አገር ነው አሁንስ የመጣኸው አትጫወትምን ብላ ስለ ጠየቀችው የመጣሁት ሶዶ ከሚባል ከተማ ከጉራጌ አገር ነው የኔ የሕይወት ነገር ብዙ ታሪክ አለውከልጅነቴ ጀምሮ መከራ አላጣኝም ምናልባት እስካሁን ድረስ ያለው የሕይወቴ ዘመን በጣም የሚበዛውጊዜ እብችግርና በመከራ ነው ያለፈው፤ እይተወለድኩበትንም አገር ምንም አረጋግጬ እንኳን ባላውቀው ጐጃም ሳይሆን አይቀርም በሕፃንነቴ ወራት ጥቂት ጥቂት አንድ አንድ ነገርም ትዝ የሚለኝ አለ ያደግሁበት አገር ግን አቶ ዲንቃ ከሚባል ነጋዴ ዘንድ አገምጃ ከሚባለው ከጉራጌ አገር ነው።

ለወዳጆቹ አንዳንድ ቀን ስለኔ ሲናገር እሰማው የነበር ይኸንን ልጅ ያገኘሁት ካባይ ወንዝ ወዲያ ማዶ ከመልካው አጠገብ እውሃው ዳር ነው። አንድ ወንድሙም ይመስለኛል አብሮት ነበር ድንገት እዚያ ወድቀው ብቻቸውን ስለ አገኛናቸው አንደኛውን ሌላው መንገኛ ይዞት ሄደ። ይኸን እኔ ይዤው መጣሁ እያለ ሲያወራ ነገሩን ገና ሳይጨርስ የቤቱዋ ባለቤት ያቶ አልዪ ሚስት ጆሮዋን ነቃ አድርጋ ከልቧ እያዳመጠች እህ እህ እያለች ነገሩን ጨርሶ እስቲናገር መጠየቅና ማዳመጥ ጀመረች።

ባሻ ጌታነህም ጨዋታውን እያከታተለ ይኸውንኑ ቃል ብዙ ጊዜ ሲአንገር ለያንዳንድ ወዳጆቹ ጌታዬን እሰማው በጣም ልብ አድርጌ አዳምጠው ነበር። አቶ ዲንቃም ሁለት ልጆች ነበሩት። ለሁሉም ለቤተ ሰቡ አገልጋያቸው እንደ ባሪያ ውሃ ቀድቼ እግር አጥቤ፤ ቤት ጠርጌ የምሠራ እኔው ነበርሁ። የቤቱ ጣጣ ሥራ ሁሉ በኔው ላይ ብቻ በመሆኑም ካቅሜ በላይ እያለ ሲናገር የቤቱዋ ባለቤት ቁና ቁና እየተነፈሰች ተመልክታ ታየው ጀመረች። ነገሩን ለማቋረጥም ባትፈልግ እስኪጨርስ አላስችልሽ አላት። ጌታነህም ወሬውን እየቀጠለ ጌታዬ አገዛዙን በታም ስላበረታብኝ አንዳንድ ጊዜም ይመታኝ ነበርና ጥቂት ከፍ ብዬ አድጌ ራሴን እምቻል እንደ ጀመርሁ ከሱ ዘንድ ጠፍቼ ኮብልዬ ያገሩ ሹም ቀኛዝማች አየለ የሚባል የብዙ ጭፍራ አለቃ ከሸዋ ተሾሞ የመጣ ሶዶ ከሚባለው አገር ላይ ነበርና እሱ ዘንድ ሂጄ በወታደርነት ለአምገልገል ገባሁ። ያም አቶ ዲንቃ ጌታዬ የነበረው ይፈልገኝ ኖሮ ከጥቂት ሳምንቶች በኋላ እዚያ ስላገኘኝ ባሪያዬ ነው ጠፍቶ ነው የመጣው እወስደዋለሁ ብሎ በዳኞቹ ላይ ከሰሰና ያዘኝ። እኔም ባሪያም አይደለሁም ብዬ በጣም ተከራከርሁ። ለጊዜውም ዳኞቹ ነገራችን ስላስቸገራቸው ቀጠሮ አድርገውልን ዋናው ዳኛ ቀኛዝማች አየለ ያገሩ ገዢ ችሎት አስቻለበት አቀረቡን። ያም ያገሩ ሹም ቀኛዝማች አየለ አስተዋይ ሰው ስለ ሆነ በብዙ ጥያቄ ምርመራውን አድርጎ ነበር። በጣምም ለኔ ያን ጊዜ የረዳኝ ያማርኛ አነጋገሬ ከሱ ከጌታዬ ካቶ ዲንቃ የተሻለ ስለ ሆነና ሁለተኛም ደግሞ በፊት እንዳገኘኝ ሰሞን የልጅነት ስሜን ጠይቆኝ ጌታነህ ነው ብዬ ነግሪው ይኸውም ስሜ የምጠራበት አልተለወጠም ነበርና ምንም ሌላ ምስክር ባይገኝም እንኳን ያማርኛ

አነገሬ ስሜ ስለ መሰከረልኝ የእውነቱ ነገር ምልክቱ ተገኝቶ ያገሩ ገዢ አቶ ዲንቃን ገሥጾ ተቈጥጦ ቀጥቶ ጌታነህ ብሎ ባሪያ የለም በማለት ካባርነት አድኖ ነጻ አወጣኝ ሲል ነገሩን ስትሰማ የቈየው የዚያው ቤት ባለቤት እናቱ ተዋበች ነበረችና ምልክቱ ካባይ ዳር መገኘቱና ስሙም አረጋግጦ ልጅዋ መሆኑን ስላስረዳት ከዚህ በኋላ ታግሣ ወሬውን ለማዳመጥ አልቻለችም። አንገቱን በጁዋ ጠምጥማ ይዛ እያለቀሰች እናትህ ተዋበች እኔ ነኝ እያለች ትጮህ ጀመር። ያም አንደኛው እንግዳ የባሶው ባሻ ካሣሁን ትልቁ ልጅዋ ነበርና ወንድሙ ነገሩን በሚናገርበት ጊዜ ሁሉ ጠርጥሮ ሲመለከተው የቈየው ካባይ ዳር እሱም መገኘቱን የወሰደው ሰው አስጠንትቶ ነበርና እኔም ካሣሁን የምባለው ካባይ ዳር የተውሰድሁት ነኝ ስላለ እሱም ትልቁ ልጅዋ ስለ ሆነ ተያየው ይላቀሱ ጀመር።

ባለቤቱም ጌታው አልዩ ይኸንኑ ታሪክ በማየት ደንግጦና ፈዞ ቈየ። እነሱም የሚያስደንቅ ስሜት አሳባቸውን ቀስቅሶት ጥቂት እየተላቀሱ ከቈዩ በኋላ እንደ ገና ወደ ልቡናቸው አሳባቸውን መልሰው የሱዋው ልጆች ሁለቱም ወንድማማቾች መሆናቸው ስለ ተገለጸ፤ እንደ ገና ተሳስመው ከብዙ ዓመት በኋላ ከእናታቸው ጋራ ስለአገናኛቸው እግዚአብሔርን አመስግነው ሲገረሙ ቈዩ። ጌታው አልዩም በዚያን ጊዜ ይህችኑ ሴት ሲያገኛት የመከራዋን ነገር ሁሉ ሰምቶ እነዚሁንም ልጆችዋን አብሮ ሲያፋልጋት የነበረው በመሆኑ ነገሩን ሁሉ እንደ ሰማ ልጆችዋ መሆናቸውን ለማመን አልተቸገረም። እናታቸውም ያን ጊዜ በተለያዩበት ቀን የደረሰባትን መከራ አባታቸውን ያባይ ውሃ ሙላት ሴውስደው ስላየች እነሱን ከዛፍ ሥር ትታ የባሏን መጨረሻ ነገር ለማየት እያለቀሰች በወንዙ ዳር ዳር እየተከተለች መሄድዋን፤ ካይኑዋ እስቲጠፋም ድረስ ውሃው ይዞት ከሄደም በኋላ ከዚያም ብትመለስ ልጆችዋን ከተወችበት ቦታ ማጣቱዋን የሆነውን ታሪክ ሁሉ እያጫወተቻቸው እንደ ገና ደግሞ ይላቀሱ ነበር። ከራትም በኋላ እንደዚሁም ልጆቹ የነበሩበት አገር ያስተዳደጋቸውን ወሬ እያመጡ ሲጫወቱ ብዙ ቈዩ።

ባሻ ካሣሁን የሚባለውን ትልቁን ልጅዋን የወሰደው አቶ ደባይ የሚባለው የሸዋ ሰው ልጅ የለውም ኖሮ ይኸንኑ ካሣሁንን እንደ ልጁ

አድርጎ ወዶትና አፍቅሮት ማሳደጉን ሲሞትም ቤቱን ንብረቱን ርስቱን አውርሶት መሞቱን ከዚያም ወዲህ በሱው እግር ለመንግሥት በወታደርነት አገግሎት ገብቶ በመልካም ሥራውና አገልግሎቱ ከሺ አንበልነት ማዕርግ ድረስ ደርሶ የጭፍራ አለቃ መሆኑን እያጫወታቸው መልካም ዕድል አጋጥሞት ከዚህ ድረስ በመድረሱ እናቱም ደስ ብሎዋት እግዚአብሔርን አመሰገነች። ባሻ ካሣሁን አቶ ደባይ ካባይ ዳር ሁለቱን ወድቀው እዚያው ካንድ መንገደኛ ጋራ እንዳገኙዋቸው ወንድማማች መሆናቸውን እየተረጠሩ ያንን ሌላ ሰው ይዞት በመሄዱ እያዘኑና እየተጸጸቱም በፊት ብዙ ጊዜም ይነግሩኝ ነበር እያለ አወራላቸው። ትንሹ ጌታነህ ግን ከባርነቱ ድኖ በወታደርነት አገልግሎቱ ከደንብ ከገባ ወዲህ በዚያው እወረዳ አገር ውስጥ አንድ አንድ ሽፍቶች ስለ ነእብሩ አንድ ጊዜ አንድ መንገደኛ ተደብድቦ ገንዘቡንም ሽፍቶች ዘርፈውት ሽፍቶቹን ፈልጎ እንዲይዝ ከሙቶ አለቃው ስለታዘዘ ጌታነህ ከባልጀሮቹ ወታደሮች ጋራ አብሮ ሄዶ ከሽፍቶቹም ጋራ ተገናኝተው ሲታኰሱ ቈይተው ሽፍቶቹ ስለ ሸሹ፤ ጌታነህ በድፍረት እየተከታተለ ለመያዝ ስለ ደረሰባቸው ተኵሰው መትተው አቍስለውት ወድቆ ኖሮ በዚያውም የተነሣ ብዙ ቀን ታሞ መዳኑን፤ ደግሞም ሌላም ብዙ አንዳንድ ችግር ከዚያም ወዲህ ያገኘውን እያጫወተ ከዚያም ሁሉ በኋላ አገልግሎቱና ልፋቱ በባልጀሮቹና በበላይ አለቆቹ ተመስክሮለት እዚሁ እሻለቅነት ማዕርግ ሹመት መድረሱን አወጋቸው። ያንለትም ሁለቱ ሳይተዋወቁ ተጣልተው ለመጋደል ደርሰው የቤቷ ባለቤት በመልካም አነጋገሩ ዋና በእውነተኛም የፍቅር ሥራዋ ሳታውቃቸው ከጠባቸው ገላግላ ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነቻቸውን ቀጥሎም እናት ሆና በመገኘቷ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እየደጋገሙ እያመሰገኑ ሲጫወቱ ከሌሊቱ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ቈይተው ወደየ ማረፊያቸው ደስ ብሏቸው ሄዱ።

በማግሥቱ ማለዳ ጧት ወታደሩ ለሥንቅ ቀለብ ይቀበላል። የደከመም ከብት እየተለወጠ ይመራል። እስከ ሁለት ቀን እዚሁ እሰፈር ውሎ ይደረጋል ተብሎ ከበላይ ሹሞቻቸው ትእዛዝ ደርሶዋቸው ልፍም ስለ ተለፈፈ እነባሻ ካሣሁን ደስ አላቸው። የእናታቸውንም ፍቅር ጥቂት

የሚጠግቡት መሰላቸው። እናታቸውም ጧት ጥቂት እረፈድ እንዳለ ቍርስ አሰናድታ ጠፍተው የተገኙትን ልጆችዋን ከየሰፈራቸው አስጠራች። ያን ጊዜም ጌታው አልፍ ሹምነቱ የመጣለትን ትእዛዝ ለማስፈጸም ወጥቶ ለጊዜውም እዚያ አልነበረም። ቍርሳቸውንም ልጆቹዋ ከተጋበዙ በኋላ አንዳንድ የንግግር ጨዋታ መሳይ አምጥተው ሲጫወቱ ጌታነህ ትንሹ ልጅዋ እናቱን ኧረ የሆነስ ሆነ እዚህ አሁን አለሸበት የምትኖሪው ተመችቶሽ ነውን? በሁሉስ ነገር ደስ ብሎሻልን? እያለ ስለ ጠየቃት ባለቤቱ መልካም ሰው ነው። ምንም የሚያስቸግረኝ ነገር የለም። እንዳልቀየምበትና እንዳይከፋኝ ተጠንቅቆ ነው የያዘኝ። በመከራዬ ጊዜም ሁሉ እናንተን ከኔው ጋራ አብሮ በመፈለግ በጣም ረድቶኝ ነበር። ብቻ ያን ጊዜ ወደዚህ ሲያመጣኝ እስላም ሳይሆን አይቀርም ብዬ በመጠርጠር ክርስቲያን ካልሆነ ሰው ጋራ አብሮ መኖር አይሆንልኝም ብለው በአጼ ዮሐንስ ዘመን ክርስትና የተነሣሁ ክርስቲያን ነኝ ስላለኝ ምንም በዚያን ጊዜ ክርስትና የተነሣው የወሎ ሰው የሚበዛው የአጼ ዮሐንስ ዐዋጅ በመፍራትም ቢሆን ይኸንኑ ምልክት ካገኘሁ በዚያን ጊዜም የተፈለመ ከሆነ እኔም እያበረታታሁ ፍጹም ክርስቲያን አደርገዋለሁ በማለት ተስፋ አድርጌ መጥቼ ነበር። እስላምነት ከልጅነቱ ጀምሮ አብሮት ያደገ ሃይማኖቱ በመሆኑ ግን በኔ ምክርና ድካም ያንን ትቶ እውነተኛ ጥሩ ክርስቲያን ለመሆን አልቻለም። አሁን ከብትም ሲታረድ ስለኔ እዳላዝንበት ክርስቲያን ሰው ተፈልጎ ነው። በዚህ ብቻ ጥቂት እንቸጋገራለን እንጂ፤ በሌላው ሁሉ ደኅና ነን እያለች ነገረቻቸው። አቶ ካሣሁን ለመሆኑ ልጅ ከሱ ወልደሻልን? ወይስ አልወለድሽም? እናት አልወለድሁም ምንም ልጅ ከሱ ባለመውለድዋ ደስ ቢላቸውም፤ በዚያን ዘመን በክርስቲያንና በእስላም መኻል ትልቅ ልዩነት ነበርና እስላም ያረደውን ከብት ክርስቲያን ክርስቲያን ያረደውን እስላም ሥጋውን አይበላም። በብዙም ነገር ሁሉ ክርስቲያንና እስላም ይልቁንም በባልና በሚስትነት አብሮ ለመኖር የማይፈቀድ እንደ ትልቅ ሆኖ የሚቈጠር በቤተ ክህነት ወገን በደንብ የሚከለከል ነበር።

አንዳንድ ክርስቲያኖች እንኳን የእስላም ሴት ለማግባት ቢፈልጉ አስቀድመው አሳምነው አስጠምቀው ክርስትና ሳያስነሱ ማግባት

አይችሉም ነበር። እስላምም እንደዚሁ ክርስቲያኗን ሳያሰልም አያገባትም። ይኸን በመሰለው ሁሉ በኑሮዋቸው አኳኋን ትልቅ የልዩነት ችግር ነበረበት። ሁለቱም ልጆቿ የጌታው አልዩን እስላምነት በመስማታቸው አሳባቸው ተለውጦ በጣም ተቈጡ። ይልቁንም ትንሹ ልጅዋ በጣም ተቈጣ። እናታቸውም ያን ጊዜ ይህንኑም ለመናገር አልፈልገችም ነበር። ነገር ግን ጥያቄ ስላበዙባትና ከዋሉ ካደሩ ወሬውን ሳይሰሙትና አንዳንድም ነገር ሳያዩ አይቀሩምና እኔው ብነግራቸው ይሻላል በማለት አስባ ነው የነገረቻቸው።

ከዚያም በኋላ እናታቸው የእስላም ሚስት ሆና ስላገኙዋት አፍረው ወደ ውጭ ወጥተው ሁለቱም ወንድማማቾች ይመካከሩ ጀመር። ምክራቸውም እናታቸውን ከአቶ አልዩ አለያይተው ወስደው ወደ ቤታቸው ተመላሽ ሰው ፈልገው ለመስደድ ይኸውም ባይሆን ከነሱ ጋራ ወደ ዘመቻውም ቢሆን ይዞ ለመሄድ ስለ ሆነ ከሱ ጋራ አብራ እንዳትቀመጥ ቊርጥ አድርገው ወሰኑ። እንግዲህ እናታችንን ስጠን ብንለው ወዶና ፈቅዶ የሚሰጠን አይመስለንም። ምክንያቱም ገልጠን እንዳንነግረው እናታችንን እንዳታለላት ለኛም ክርስቲያን ነኝ ለማለት ይሞክር ይሆናል። ይኸን ያህል ዓመት ተለያይተን ቈይተን አሁን እግዚአብሔር ካገናኘን ከእንግዲህ ወዲህ ልባችን እያወቀ እሱ ዘንድ እንድትቀመጥ የምንፈቅደውና የምናስበው አይደለምና እናታችንን ስጠን እንበለው ፈቅዶ ቢሰጠን መልካም ነው። ግን እንቢ የሚለን የሆነ እንደ ሆነ፤ በዳኛ ከሰን በግድ አለያይተን እንወስዳታለን። ለዚህ ካበቃን እናታችን ከእስላም ጋራ መኖር አትችልም ብለው ተነጋግረው ጨርሰው እነሆ ስለዚሁ ጕዳያቸው ጌታው አልዩ እውጭ ሥራው አርፍዶ ወደ ቤቱ እንደ ተመለሰ፤ ሻለቃ ካሣሁንና ጌታነህ እሱ ካለበት ዘንድ ሄደው ተገናኝተው እንግዲህ እግዚአብሔር ካገናኘን እናታችንን ወደኛ ዘንድ ለመውሰድ እንፈቅዳለንና ስጠን ብለው ጠየቁት። አቶ አልዩም ይህንኑ ስላሉት ደንግጦ ምነው ወንድሞቼ ይህን ያህል ዓመት አብራኝ ኖራ ቤቴም ወግ ማዕርግ ያገኘው እሷ ከመጣች ወዲህ በእሷዋው ነው የበደልኋትና ያስቀየምኋትም ነገር ያለ አይመስለኝም። ሳገኛትም በመከራዋ ጊዜ ሁሉ

እናንተንም በመፈለግ በተቻለኝ ዐቅሜ ረዳኋት ምስክሬም እሳዉ ነች። አሁንስ በደኅና በመገናኘታችሁ ደስ ብሎን ሳለ እንደዚህ ያለውን ነገር ምነው አመጣችሁብኝ? ደግሞም ወደ ዘመቻ በመሄድ እመንገድ ላይ ነው ያላችሁ ለሁሉስ ነገር በደኅና በሰላም ለመመለስ በቅታችሁ በኋላ እሷንም ጠይቀናት ባትፈቅድ ያን ጊዜ ቢሆን አይሻልም ብሎ ቢጠይቃቸው እሺ ሊሉት አልፈለጉም። ከእንግዲህ ወዲህ እናታችን ከኛ እንድትለይ አንፈቅድም ስለ ዘመቻውስ ቢሆን ሴቶች አብረው የሚጓዙ ሞልተው የለምን ንጉሣችን አጼ ምኒልክስ ባለቤታቸውን እቴጌ ጣይቱን ይዘው ይኸው ወደ ዘማመቻው ተነሥተው የለምን እኛስ እናታችንን ይዘን ብንሄድ ምን የሚያስቸግረን ነገር አለበት ይልቅስ ስጠንና ይዘን እንሂድ እያሉ ስላስቸገሩት አቶ አልዩም በግድም ቢሆን ለመውሰድ መፈለጋቸውንና መፍቀዳቸውን ስለ ተረዳው እሷ ሳትጠላኝና መሄድ ሳትፈልግ እኔ ወድጄና ፈቅጄ ቤቴን አፍርሼ የብዙ ዘመን ሚስቴን ልሰጣችሁ አልችም ብሎ ቍርጥ ምላሽ ስላስታወቃቸውና እነሱም እንደዚሁ ባለው ጥያቄና ልመና እይማይሰጣቸው መሆኑን አይተው ስለ ተረዱት የጦር አበጋዙና ያገሩም ዋና ዳኞች ወዳሉበት ለመክሰስ ደሴ ከተማ ሄዱ።

ባሻ ካሣሁንና የሻለቃ ጌታነህ ደሴ ከተማ ወደ ጦሩ አበጋዝ እንደ ደረሱ ያን ጊዜም የራስ መኰንን ዋናው አጋፋሪ ፊታውራሪ በላይ ከወሎ ገዢ ከራስ ሚካኤል ዳኞች ጋራ አብሮ ተቀምጦ ችሎት ያስችል ነበር፤ ማስቻሉም ዘማቹ ወታደር በሚያልፍበት አገር ላይ ባላገሩን እንዳይዘርፍ ከብቱንም እህሉንም እንዳይነካ ዐዋጅ አስቀድሞ ተነግሮ ነበርና አንዳንድ ወታደሮች ያዋጁን ቃል እየጣሱ የባላገሩን እህል ሲዘርፍ ከብቱን ሲነዱ እየተገኙና እየተያዙ እነዚሁም ከዋናው ከጦር አበጋዝ አጋፋሪና ከዳኞቹ ዘንድ እየቀረቡ ከብቱ እህሉ ለሄደበት ባላገር እያስመለሱ ዐዋጅ የጣሱትንም ወታደሮች ይቀጡ ነበርና ሁለቱ ወንድማማችም እነሻለቃ ጌታነህ ተራ እስኪያገኙ ድረስ ሲጠባበቁ ቈይተው ያን ጊዜም አንዳንዶች ወታደሮች የቀረቡት ተፈርዶባቸው ካለቀ በኋላ እነዚሁም ወደ ዳኞቹ ቀርበው ላዳኞቹ እናታችን ጠፍታ ስትኖር አሁን አንድ ጭቃ ሹም ቤት

አግኝተናት እናታችንን ስጠን ብንለው እንቢ ብሎ ከለከለን፤ አሁን እኛ የምናመለክተው እሱ እናታችንን ይዞ ቀርቦልን እንቢ የሚልበት ነገር ተጠይቆ እናታችንን እንዲሰጠን ነው ብለው ነገራቸውን አጠር አድርገው አቀልጥፈው አመለከቱ።

ዳኞቹም አንዱን ከልካይ ጠርተው አዘው ለነገ ያው ጭቃሹሙ እናታቸውን ይዞ እንዲቀርብ ቀላጤ ሰጥተው የሚገባውንም ለቀላጤው ከፍለው እነባሻ ጌታነህ ይዘውት ሄዱ፤ በሩ ሜዳም እንደ ደረሱ ቀላጤው ጌታው አልዩን አስጠርቶ እናት የተባለችውን ይዞ ነገ ጡዋት ደሴ ከዳኞቹ ዘንድ እንዲቀርብ ዳኞቹ ማዘዛቸውን በምስክሮች ፊት አስታውቆ ነግሮ ተመልሶ ሄደ።

በማግስቱም ዐርብ ቀን ስለ ነበረ ራስ ራስ መኰንን አንዳንድ የተበደለ ድኻ ዳኞች ፈርደውበት ይግባኝ ያለ ነገሩን ለበላይ ደግሞ ለማስታወቅ ይሰማልኝ ያለ ሰው እንዳለ እንደ ገና ለማየት ባይኖርም የቀረበውን ማንኛውንም አቤት ባይ ከዳኞቹ ከመኳንንቱ ጋራ አብረው ለማየት በቤተ መንግሥቱና በያውራጃው አገረ ገዢዎች ዘንድ እንደ ተለመደው ያርብና የሮብ አደባባይ ተቀምጠው ችሎት ማድረግ እንደዚሁም በዘመቻውም ግዚኤ በመንገድ ላይ ውሎ ባደረጉበትና አጭር መንገድ በተጓዙበት ቀን ሰዓቱ ጥቂትም ቢሆን በተለመዱት ሮብና ዐርብ ቀኖች ችሎት እያስቻሉ አንዳች የበደል ነገር የደረሰበትን ሰው እየሰሙ ብይንና ፍርድ ያደርጉ ነበርና ያንለትም ቀኑ ዐርብ ስለ ሆነ፤ ዳኞቹና ብዙ መኳንንቶቹም ባሉበት እሳቸው ራሳቸው ችሎት አስችለው ተቀምጠ አንዳንድ ባለነገሮች እየቀረቡ ነገራቸው ከታየ በኋላ፤ ያን ጊዜም ጌታው አልዩ እናታቸውን ይዘህ ቅረብ ተብሎ የዳኞቹ ቃል ስለ ሄደበት ሚስቱን ይዞ መጥቶ የመቅረቢያው ጊዜ ስለ ደረሰ አጋፋሪው ፊትታውራሪ በላይ እዚያው ከሥራው ላይ በስተ ግንባር ወገን ቆሞ ከሳሹን በቀኝ ተከሳሹን በግራ እንዲሆኑ በደንቡ እያደረገ ባለነገሮቹ ክሳቸውን እያመለከቱ እያታወቁ ተከሳሹም እየመለሰ ይነጋገሩ ነበርና።

ባሻ ካሣሁንና የሺ አለቃ ጌታነህ ያቶ አልዩ ከሳሾች በደንቡ ተቃርበው የክሳቸውን ነገር ማስታወቅና ማመልከት ጀመሩ። ያን ጊዜም ሲናገሩ

እናታቸውን ለመውሰድ ያሰቡበት እስላም በመሆኑ ምክንያት መሆኑን ለመግለጥና ለመናገር ስለ ሁለት ነገር አልፈለጉም። እስላም ነው ብለን ብንናግር በአጼ ዮሐንስ ዘመን ክርስትና ተነሥቻለሁ ክርስቲያን ነኝ ስለሚል አጉል ጭቅጭቅ ያበዛብናል በማለት ሁለተኛም እናታቸው የእስላም ሚስት ሆና መቈየትዋን በዚያ በሸንጎ አደባባይ ላይ ነገሩን መግለጥ እንደ ነውር መስሎ ስለ ታያቸው የሃማኖትን ጉዳይ ማንሣቱን ቸርሰው ትተው እናታችን ጠፍታ ከኛ ተለይታ ብዙ ዘመን ኑራ አሁን እሱ ዘንድ አግኝተናት ስጠን ብንለው እንቢ ስላለን ስለዚህ ነው አመልክተን ከሰን ያስመጣነው አሁንም እናታችንን እንዲሰጠን ነው የምንሻው ብለው አጠር አድርገው ክሳቸውን አመለከቱ።

ጌታው አልዩም መልሱን ስጥ ስለ ተባለ እሱም እነዚህ ሁለት ሰዎች ከትናንት በስቲያ በጭቃ ሹምነቴ የታዘዝኩትን መስተንግዶ እዚህ ለማሰከብ አሲዤ መጥቼ ሳለሁ እነኢ ቤት ግቢ መጥተው እኔ እሰፍርበታለሁ በመባባል እነሱ ሁለቱ ተጣልተው ጭፍሮቻቸውን ይዘው ተሰላልፈው ከመጋደል ደርሰው ተጩሆ መንደሩ ሁሉ በዚያ ዙሪያ ያለው ተሸብሮ እሷ ባለቤቴ ወጥጣ ገላግላ ለሁለቱም መስፈሪያ ቤትና ቦታ አሰጥታ እኔም ተመልሼ ስደርስ ሰላም ሆኖ ስለቈየኝ እሱዋ የሠራችውን ደኅና ነገር ሁሉ ሰምቼ ደስ ብሎኝ አመስግኜት ለከብታቸው ጭድና ገፈራውን፤ ለሰዎቻቸውም የተገኘውን እህልና ውሃ ሰጥተን ማታም ራት በምንበላበት ጊዜ ሁለቱንም ጋበዝናቸው መጥተው በደኅና በልተን ጠጥተን ሄደው አድረን ሳለን ጡዋት መጥተው የኻያ አንድ ዓመት ሚስቴን እናታችን ናትና ስጠን ስላሉኝ ሁለታችሁ ትናንትና ሳትተዋወቁ በጠብ ተገናኝታችሁ ዛሬ ደግሞ እሷን እናት አድርጋችሁ የቤቴን ባለቤት ሚስቴን ለመውሰድ አትችሉም ደግሞም ዛሬ ያላችሁት በዘመቻ ላይ በመንገድ በመሆኑም በደኅና በተመለሳችሁ ጊዜ ነገር ቢኖራችሁ ያን ጊዜ እንነጋገራለን ብላቸውም በግድ ብለው እሱዋ ሳትጠላኝ ተከስሼ የመጣሁት ስለዚህ ነው ብሎ የክሱን መልስ አመለከተ።

ልጆች እናታችን እርግጥ እሱዋው መሆንዋን ምንም የተለያየንበትም ጊዜ በረዝም ዐውቀናል ታሪካችን እጅግ ብዙ ነው፤ ይኸንኑም እውነት

መሆኑን ለማስረዳት እሱዋን እናታችንን ከመጀመሪያው ጀምሮ የሆነውን ነገር ሁሉ ብትጠይቋት ከኛ ይልቅ እሱዋ ደኅና አድርጋ ለማስታወቅ ትችላለች፤ አሁንም በድንገት ባጭር ጊዜ ውስጥ የተዋወቅነውና የተገናኘነው እግዚአብሔር በተአምሩ ኀይሉን በመግለጽ ነው፤ ከናታችን ስንለያይ በጣም ትንንሽ ልጆች ነበርን ስለ ሁሉም ነገር እሷው ብትጠየቅ ይሻላል ብለው አመለከቱ።

ይኸ ሁሉ ንግግር ሲሆን ከማኻከላቸው የቆመው አጋፋሪ ፊታውራሪ በላይ የሱ የጣጣ ነገር እንዳለበት ያወቀውና የጠረጠረው ያሰበውም በጭራሽ አልነበረም። ነገራቸውን ብቻ በደንብ በየተራ እንዲነጋገሩ ለሌላው ሁሉ እንደሚያደርገው በጌታው በራስ መኰንን ፊት የሥራውን ተግባር ያስተናብር ነበር። ያን ጊዜም ከዳኞቹ አንዱ ተነሥቶ ነገሩን ሁሉ እንዲነጋገሩ የተፈቀደላቸው እንደሆን እጅግ የሚረዝም ስለ መሰለው ለማሳጠር በቀጥሮ ለማቈየት ፈልጎ አሁን እናንተም እዘመቻ እመንገድ ላይ በመሆናችሁ ለሱም ብዙ ዘመን አብራው የኖረች ሚስቱ ናት ስለሚባል ተዋውሳችሁ ቈይታችሁ በደኅና በተመለሳችሁ ጊዜ ነገሩን ብናየው አይሻልምን እይሚያስቸኵል ነገር አሁን እንደ ሰማነው ያለበት አይመስለንም ብሎ ልጆች የተባሉትን ስለ ጠየቃቸው፤ ልጆቹም ባሻ ካሣሁንና የሻለቃ ጌታነህ ሌላም አንዳንድ ነገር ለጊዜው ለማስታወቅ ያልፈቀድነውም አይጠፋም። እናታችን ከእግንዲህ ወዲህ ካልተፈረደብን በቀር ወደን ከሱ ጋራ እንድትቈይ የምንፈቅደው ነገር የለም። ስለዚህ እሱዋኑ ልጆቹዋም እንደሆንን የሚያስረዳውን ነገር ብትጠይቋት እውነቱን ሁሉ ለመረዳትና ለማወቅ ብዙ ጊዜም፥ የሚወስድ አይመስለንም። የምንለነምነውም አሁን ነገሩን ሰምታችሁና አይታችሁ እንድትሰጡን ነው ብለው አመለከቱ።

ራስ መኰንንም ነገራቸው እንዲሰማና ፍርድ እንዲሰጥ ስለ ፈቀዱ ዳኞቹም መልካም ነው እሱዋው እናት የተባለችው ተናግራ ብታስታውቀን ይሻላል ብለው ስለ ጠየቁዋት ታሪኩን ሁሉ ከሥር ጀምሮ እስከ ጫፉ እንድታስረዳ የግድ ሆኖባት ለማስትወቅ ጀመረች። እሱዋም ያን ጊዜ አገሩዋ ጐጃም የነበረችበትም አገር ከኻያ አንድ ዓመት በፊት አነደድ

ከሚባለው ወረዳ አገር ውስጥ ያን ጊዜም በሕግ የተጋባችው አቶ በላይ የሚባል ባል እንደ ነበራት ከሱም እነዚህን ሁለት ልጆች እንደ ወለደች ስትናገር ፊታውራሪ በላይ አጋፋሪው ይህን ቃል ሲሰማ በጣም ደንግጦ ከመኻከላቸው ቆሞ ነበርና ዘወር ብሎ እሱዋን አስተውሎ እየተመለከተ ነገርዋን እስክትጨርስ ድረስ ነቅቶ እያዳመጠ አንዳንድ ጊዜም ወደ ከሳሾቹ ሰዎች እየዞረ ትኩር አድርጎ እያየ ያስተውላቸው ጀመር።

እሱዋም ነገሩዋን እያከታተለች በዚያን ጊዜ አንድ ገባራችን የሆነ ሰው የባሌን ርስትና ጉልት ከራስ አዳል በኋላ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከተባሉት የጐጃም ገዢ ለምኖ እኛን አስነቅሎ እሱ ተሾሞ ስለ መጣ ባሌ አቶ በላይ እንግዲህ ለገባሬ ገባር ሆኜ ምንም ቢሆን በዚህ አገር አልቀመጥም ወደ ሸዋ ሂጄ ትዳሬን እፈልጋለሁ ብሎ፤ እኔንና እነዚህን ሁለት ልጆቹን ይዞ በሌሊት ተነሥተን ጠፍተን ጉዞዋችንን ያዝን። በዚያን ጊዜም ይኸ ትልቁ ሰባት ያኛው ትንሹ አምስት ዓመታቸው ነበር።

በደጀን በኩል ነበርና የተጓዝነው ቊልቊለቱን ወርደን ዐባይ ወንዝ ከመልካው እንደ ደረስን ድንገተኛ ዝናብ ወደ ላይ ዘነበ። ጊዜውም እንኳን የበጋ ወራት ነበር፤ ውሃው ሞልቶ ስላገኘነው ካሁን አሁን ጐድሎልን እንሻገራለን ብለን ቈይተን ሳለ፤ ጥቂት ሙላቱ እንደ መጕደል ሲል ባሌ ከኋላ መንገደኛ መጥቶ የሚያውቀውን ሰው እንዳያገኘንና እንዳያየን ቸኵሎ ነበር። ውሃ ዋናም መዋኘት ደኅና አድርጎ ስለሚያውቅ አስቀድሜ እኔ ገብቼ ሞክሬው እናንተን ደግሞ ተመልሼ እሻገራለሁ ብሎ ገብቶ እየዋኘ በደኅና ከማዶ ደርሶ ተመልሶ ሲመጣ ወደ መኻሉ ሲደርስ እንደ ገና ትቅል የውሃ ጐርፍ ተወደላይ ተጨምሮ መጥቶ ስለ ደረሰበት፤ ምንም እየዋኘ ጥሶ ለማለፍ ቢጣጣር የማይችለው ሆኖ ወራጁ ሙላት አሸንፎት ከመልካው አሳስቶ ጥቂት በጥቂት እያዋረደ ይዞት ሲሄድ ስላየሁ እነዚህን ልጆች አንድ ዛፍ ጥላ ሥር ትቼ እየጮሁና እያለቀስሁ በወንዙ ዳር እየሄድሁ ካሁን አሁን ይወጣ ይሆን እያልኩ ስከታተል ብዙ መንገድ ከሄድኩ በኋላ ላይኔ ጠፍቶ ውሃው ይዞት ሲሄድ አየሁ። እዚያ እበረሃ አገር ብቻዬን ሳለቅስ ስጮህ ቈይቼ ወደ ልጆቼ ብመለስ እነሱንም ደግሞ ከዚያው ከተውሁበት ቦታ አጣኋቸው። አውሬ በልቷቸው ይሆን በማለት

የተንጠባጠበ አገኛለሁ ብዬ ብሻም ምንም ሳላገኝ ቀረሁ። ወዲያም ወዲህም እየባከንሁ ብፈልግ አንድም ምልክት አጣሁ። ተመልሼ ግን ወደዚያው ስመጣ ወንዙን ተሻግረው የሄዱ ባለከብት መንገደኞች ከማዶ በሩቅ አይቼ ነበርና ፈልጌም ካጣኋቸው ወዲያ ልጆቼን ምናልባት እነዚያ ሰዎች ወስደዋቸው ይሆን ብዬ መጠርጠር ጀመርሁ።

ውሃውን ግን በእግር ተሻግሬ ለመከታተል የማልችል ሆኜ እዚያው እያለቀስሁ፤ እየተንቀጠቀጥሁ ይህ ሁሉ መከራ ባንድ ጊዜ ስለ ደረሰብኝ የማደርገውን ነገር አጥቼ አእምሮዬ ጠፍቶ ደክሜ ወድቄ ነበረ እያለች ስትነገር፤ ባደባባይ የነበረው ሰው ሁሉና ዳኞቹም ይኸን መከራ የሞላበት ታሪክኋን እያዳመጡ በመስማት አሳባቸው ተናውጦ፣ የምታነገረውን መጨረሻ ለመስማት በሚያስደንቅ ዝምታ ወደሱዋው እየተመለከቱ ነገሩዋን ከልብ ያዳምትጡዋት ነበር። ያ ኢጋፋሪው ፊታውራሪ በላይ ግን ይኸን ሁሉ የደረሳባትን መከራ ያን ጊዜ በመስማቱ ምንም የነገሩዋን መጨረሻ በታላቅ ትዕግሥት ለማወቅም ቢጠብቀው አንዳንድ ጊዜ በማልቀሱ ዕንባው እየወረደ እንዳይታወቅበት በልብሱ ጫፍ ዝግ ብሎ ዐይኑን እየተራረገ እንዲሁ ነገሯን ይሰማ ነበር።

እሱዋም ታሪኳን እየቀጠለች በማውራት ቀኑ መሽቶ በሞትና በሕይወት ማኻል እዚያ ወድቄ ሳለሁ፤ ማታ በጨለማ መብራት አብርተው ሰዎች መጥተው ከዚያ ቦታ አንሥተው ሲወስዱኝ እንደ ሕልም መስሎ ይታወቀኝ ነበር፡ ወደ ሰፈራቸውም ተሸክመው ወስደው ካደረሱኝ ወዲያ አንድ ቦታ አስተኝተውኝ ተልባ መሳይ በማር በጥብጥው ካጠጡኝ በኋላ፣ ነፍሴን ማወቅና ትንፋሼንም እንደ ልቤ መተንፈስ ጀመርሁ። ያን ጊዜም እህል ቢያቀርቡልኝ ለመብላት አልቻልሁም። ከወደቅሁበት አንሥቶ ይኸን ሁሉ ርዳታ ያደረገልኝ ይኸው ጌታው አልዪ ነበር። በማግሥቱም ጥዋት ስለኔው አስቦ አንቺ ሴት አገርሽ ወዴት ነው ያገኘሽስ ነገር ምንድነው አሁንስ ወዴት ለመሄድ ነው የምታስቢው ብሎ ስለ ጠየቀኝ የመጣሁት ከሩቅ ቦታ ከባሌና ከልጆቼ ጋራ ነበርኩ እዋኛለሁ ብሎ ገብቶ ባሌን ውሃው ስለ ወሰደብኝ ልጆቼ ሕፃናቶች ስለ ሆኑ እዚህ ትቻቸው የባሌን መጨረሻ ለማየት ሄጄ ነበር። ብመለስ እነሱንም አጣኋቸው በሩቅ ግን

እማዶው ወንዙን ተሻግረው የሄዱ መንገደኞች ስመለስ አይቼ ነበርና ምናልባት ልጆቼን የወሰዱዋቸው እነዚያ ይሆናሉ በማለት ልቤ ይጠራጠራል። እነሱን ለመፈለግ ለመሄድም የማስበው ወደዚያው ነው ብዩ ስላመለከትሁት ወንዙንም በከብት አሻግሮ ልጆቼን ሲያፈላልገኝ ሰንብቶ ምንም የደረሱበትን ወሬ የሚያመለክተንና ሚያስታውቀን ስላላገኘን ተስፋ ቈርጬ ወደ እንጦጦ አብሬ ከሱ ጋራ መጣሁ።

እዚያም እንጦጦ እንደ ደረስን የማውቀው ሰው አልነበረምና እንዲሁ ሥራና ጌታ ለኑሮዬ እየፈልግሁ ጥቂት ቀኖች ከቈየሁ በኋላ፤ ጌታው አልዩ ወደ አገሩ ወደ ወሎ የሚሄድበት ቀን ስለ ደረሰ፤ ወደኔ ዘንድ መጥቶ እዚህ አገር ያምታውቂው ሰው እንደሌለሽ አያለሁ፤ እኔም ብቻዬን ያለውሁ ሰው ነኝና ፈቃድሽ ቢሆን ከኔ ጋራ ሄደሽ አብረን መኖር እወዳለሁ ብሎ ስለ ጠየቀኝ፤ ምንም እንኳን የምወደውን ባሌንና ልጆቼን ሁሉ አጥቼ ሌላ ባል አግብቼ ደስታ ለማድረግ ፈቃዴም ባይሆን፤ ለጊዜው የሕይወቴን ኑሮ የማሳርፍበት አንድም ተስፋ ያለው ነገር ስላልነበረኝ፤ ደግሞ እዚህ ብቻዬን ቀርቼ ሌላ መከራ ያገኘኝ ይሆናል ብዩ በመፍራት እሺ ብዩ ፈቃዱን ፈጽሜ አብሬው መጣሁ። ከሱም ከተገናኘን ወዲህ ያስቀየመኝና የበደለኝ ነገር የለም ከተገናኘንም ይኸው እሱ እንደተናገረው ወደ ሐያ አንድ ዓመት ሆኖዋል። ከልጆቼ ጋራ ግን በቀደም እመተዋወቅ የደረስነው በድንገት ነው። ይኸው ዛሬ ሦስተኛ ቀን መሆኑ ነው። እግዚአብሔር በረቂቅ ሥራው ወደኔ ዘንድ ልኳቸው ኖሮ ሁለቱም ልጆቼ እርስ በርሳቸው ሳይተዋወቁ እኛ ግቢ ለመስፈር መጥተው ያንኑ መሳፈሪያ እኔ ነኝ የቀደምኩና የያዝኩት በመባባል ብርቱ ጠብ ተጣልተው ሊታኰሱና ሊጋደሉ ጥቂት ቀርቷቸው ጌታው አልዩ ለጊዜው እዚያ አልነበረምና የሆነውን ጠብና ሽብር እግቢያችን አጠገብ ስለሰማሁ ከሰዎቼ ጋራ እኔው ራሴ ወጥቼ ከነሱ ተገናኝቼ ወንድሞቼ ቦታው ለሁላችን ይበቃል ላንድ ቀንና ለሁለት ቀን መሳፈሪያ ብላችሁ አትጣሉ ብዩ ለምኜ ገላግዩ ለሁሉም ቦታ እንዲያገኙና እንዲሰፍሩ አደረግሁ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ልጆቼ መሆናቸውን እንኳንስ ላውቀው አሳቤ እንኳ የጠረጠረው ነገር አልነበረም። ማታ ግን አቶ አልዩ ከሥራው ተመልሶ መጥጦ በራት ጊዜያት

ሁለቱን እንግዶች ሹሞች ከኛው ጋራ እንዲጋበዙ ስለ ፈለግን ከየሰፈራቸው አስጠርተን መጥተው አብረን ሁላችንም አንዳንድ ነገር እያመጣን እየተጨዋወትን ስንበላ፤ ይህ ትንሹ የሕይወቱን ታሪክ ረዘም ያለ ነገር አምጥቶ ከልጅነቴ ጀምሮ መከራ አላጣኝም እያለ ያገኘውን መከራ ሁሉ ሲያወራን የኔው ልጅ መሆኑን የሚያመለክትና የሚያረጋግጥ ነገር አገኘሁ። በነገሬም ብዛት አሁን የማሰለች ባይሆንብኝ ለፍርዱ እንዲመቻችሁ በምን አኳኋንና ምልክት ነገሩን እንዳረጋገጥሁ ለማስታወቅ እወድ ነበር ብላ አመለከተች።

ራስ መኰንንና ዳኞቹም ምንም በነገሩ ብዛት ሰዓቱ እንኳን ቢተላለፍ የነገሩን ሁናቴ ሁሉ በዝርዝሩ ጨርሶ ለመስማት ስላሳሰባቸው እንድትናገር ፈቀዱላት። እሱዋም ይኸ ትንሹ የሕይወቱን ታሪክ ሲነግረን ያሳደኛ አንድ የጉራጌ ነጋዴ አቶ ዲኒቃ የሚባል ያገምጃ ሰው ነበር። ለያንዳንድ ወዳጆቼ ስለኔ ሲናገር ይኸንን ልጅ ካባይ ወንዝ ማዶ እወንዝ ዳር ወድቆ አግኝቼ ነው ያመጣሁት ሁለት ነበሩ አንደኛው ሌላ መንገደኛ ይዞት ሄደ እያለ ሲያወራ በጣም ልብ አድርጌ እስማው ነበር። ይኸውም ጌታዬ እንደ ባሪያ እያሠራ እጅግ መከራ ያሳየኝ ነበርና ጥቂት ከፍ ብል አድጌ ራሴን መቻል ስጀምር፤ ከሱ ዘንድ ጠፍቼ ኮብልዬ ወደ ዋናው የጉራጌ አገረ ገዢ ከተማ ሶዶ ሄጄ ወታደርነት ገባሁ እያለ ሲናገር ስለ ሰማሁት ሁለት ነገሮች ምልክት የሚሆኑ አገኘሁ። ዐባይ ወንዝ ዳር በመገኘቱና ሁለት ነበሩ የተባለውን ይኸንንም ሁሉ ሲናገር ዝም ብዬ አዳምጠው

ወዲያውም ጨዋታውን ቀጥሎ ያም ጌታዬ አቶ ዲኒቃ ስለ ጠፋሁበት ይፈልገኝ ኖሮ እዚያው መጥቶ ስላገኘኝ በዳኞቹ ላይ ክሶ ባሪያዬ ነው ብሎ ያዘኝ እኔም ባሪያም አይደለሁም ብዬ ተከራከርሁት። ከብዙም ምርምር በኋላ የልጅነት ስሜ ጌታነህ የሚባለው ስላልተለወጠ ያማርኛ አነጋገሬም የተካከለ ስለ ነበረ፤ በዚሁ በሁለቱ ምክንያት ዋናው ዳኛ ከባርነት ነጻ ሊያወጣኝ ቻለ ብሎ ደግሞ ሲናገር ስለ ሰማሁት ትንሹ ልጄ ጌታነህ ነበረና ይኸም ስሙ ሦስተኛ ምልክት ሆኖኝ ልጄ መሆኑን አረጋግጬ ዐወቅሁት። ወዲያውም ያም ሁለተኛው እንግዳ ይኸንኑ ወሬ ሲሰማ ቈይቶ ነበርና እኔም ካሣሁን የምባል ካባይ ዳር ከወንዙ ወዲያ ማዶ ወድቄ የተገኘሁ

ነኝ። ያሳደገኝ አቶ ደባይ የሚባለው የባሶ የሸዋ ሰው አንዳንድ ጊዜ ይነግረኝ ነበር። ሁለትም እንደነበርን፤ አንዱንም ሌላ መንገደኛ በመውሰዱ፤ እሱ ሁለታችንንም ለመውሰድ ባለመቻሉ እያዘነ ብዙ ቀን ሲነግረኝ ነበር። ምናልባት እኔም ስሜም ካሣሁን ከልጅነቴ ጀምሮ የምጠራበት ነው። ይኸውም ሁሉ ነገር ልጅሽ መሆኔን እሱም ወንድሜ መሆኑን ያረጋግጥልን ይሆናል ስላለኝ፤ ስማቸው ጊዜው፥ ዕድሜያቸው ሁሉ ምስክር ሆኖልኝ ልጆቼ መሆናቸውን ጨርሼ ያመንኩበት ስለዚህ ነው ብላ ነገሩን ከመጀመሪያው ጀምራ እስከ መጨረሻው አስታወቀች። ይኸውም ነገር ባደባባዩ የነበረውን ሰው ሁሉ በጣም አስደነቀ። ወዲያውም አንዱ ዳኛ አቶ አልዩን ይኸ አሁን ሚስትህ የተናገረችው ነገር ሁሉ የሐሰት ነገር አለበት ወይ ብሎ ስለ ጠየቀው፤ ምንም ሐሰት የለበት፤ ሁሉም አሁን የተናገረችው፤ ከኔም ጋራ ከተገናኘን ወዲህ የሆነው እውነት ነው። እነዚህም ራታችን ላይ ጨዋታ ጀምረው ሲናገሩ እናታቸው መሆንዋን ዐውቀው አልነበረም፤ በውነት ልጆችዋ መሆናቸውን በሰማሁት ነገር ሁሉ እኔም ተረድቸዋለሁ፤ አሳቤም አምኑዋል። እሱዋን እንወስዳለን በማለታቸው ብቻ ነው ከኔም ጋራ የተጣላነው እያለ አመለከተ። ይኸው ሁሉ ሲሆን ራስ መኰንን ፊታውራሪ በላይ አጋፋሪያቸውን ከሌላው ሰው ሁሉ ይልቅ አሳቡ እንደ ተነካና አንዳንድ ጊዜም ዕንባው ሲፈስ ልብ አድርገው ተመልክተውት ቈይተው ነበርና ይኸንኑም ፊታውራሪ በላይን ስለሚወዱት ፊታውራሪ በላይነህ ይሉት ነበርና ያን ጊዜም በዚሁ ስሙን ጠርተው ይኸ የሰማነው ነገር ባደባባዩ ያሉትን ሰዎችና ዳኞችንም ሁሉ የሰጠን ስሜት ታላቅ ነው። ነገር ግን ከሁሉም የሚበልጥ ደግሞ ያንተ አሳብ ስሜት በጣም ተነክቶ አይሃለሁ። መጨረሻውን የእግዚአብሔር ኀይል እንዲህ እያሳመረ እያገጣጠመ ሲገልጠው ምን የሚያሳዝንህ ነገር አለ ስላሉት፤ እሱም ልዑል ጌታዬ ሆይ ታሪኩ ገና መቼ አለቀ። አሁንም ደግሞ ገና የሚሰሙት ነገር አለ። ከርስዎ ጋራ ያገናኘኝን እግዚአብሔርን አመሰግናሁ። ካገኘሁዎ ጀምሬ ብዙ ትምህርት ከርስዎ አጥንቻለሁ። ለድኾች ስለሚራሩ አንዳንድም ጉዳታቸው ቶሎ እየተሰማዎ ከኀይለኞች ከግፈኞች፥ ከትዕቢተኞች ለማዳን በኀይል እየተቃወሙ ሲሠሩ፤ በመልካም ነገርም ሰውን ድስ ለማሰኘት ሲጣጣሩ እግዚአብሔር ሲፈሩ

የሰዎች በመልካም ነገር ደስታቸው ደስታዎ ኀዘናቸውም ኀዘንዎ መሆኑን ዘወትርም በማየቴ ወደ እርስዎ ዘንድ እግሬን የመራውን አምላኬን አመሰግነዋለሁ። ይኸው እርስዎ ዘንድ ከገባሁ ወደ ኻያው ዓመት ሆኖኛል። ሁል ጊዜም መልካሙን እምነትዎና ግብርዎን በማየቴ ያረጀው ሰውነቴ ታድሶዋል።

እንኳንስ ተሹሜ ማዕርግ አግኝቼ በዕለት ቀለብና ባመት ልብስም ብቻ ቢሆን እንደርስዎ ካለ የሰው ኀዘን ቶሎ ከሚሰማው ሰው ጋራ መኖር ታላቅ ዕድል ነው እያለ የምስጋና ቃል ብዙ ሲናገር ቈይቶ ነበር።

ያንጊዜም ተቀማጩም ሆነ ቋሚውም እዚያ አደባባይ ጉባኤ የነበረው ሰው ሁሉ ሲነገር ከቈየው የክስ ነገር ውስጥ ፊታውራሪ በላይ ያለበት መሆኑን እንኳንስ ያወቀና የጠረጠረም አንድም አልነበረም። ወዲያውም ፊታውራሪ በላይ ለዳኞቹ ይህች ሴት እስካሁን ስትናገር በምንሰማው ልጆችዋን አረጋግጣ ለማወቅ የቻለችው ምንም ሌላ ተጨማሪ ነገር ቢኖረው ስማቸውን ካወቀች በኋላ ነው። እነዚሁም ከሳሾችና ተከሳቾችም ተቃርበው እስካሁን ሲነጋገሩ የሴትዮዋ ስም ተጠርቶ አልተሰማም ስለዚህ እኔ አሁን በስሙዋ እንድጠራት እንዲፈቅድልኝ እለምናለሁ ብሎ ስለ አመለከተ፤ ለጊዜው ይህ አነጋገሩ በምን ምክንያት እንደ ሆነ ይኸን ያለንበትን ስላላወቁት ዳኙኞቹን ጥቂት አስቸግሮዋቸው ዝም ብለው ቈይተው ሳለ አንዱ ዳኛ ተነሥቶ ነገርዎ ይኸን የሚሉበት አልገባንም አላወቅነውም ቢሆንም ግን የሱዋን ስም ካወቁት እንዳሰቡት ቢናገሩም የሚጎዳ ነገር የለበትም ብሎ መልስ ስለ ሰጠው ፊታውራሪ በላይም በዚያን ጊዜ ወደ ሴትዮዋ ዘወር ብሎ ተመልክቶ ወይዘሮ ተዋበች ይህ ስም ስምሽ አይደለምን ብሎ ስለ ጠየቃት፤ ይኸንንም የጠየቀበት ምክንያት ለምን እንደ ሆነ እሱዋም ሳታውቀውና ሳትረዳው ወደ ዳኞቹ እያየች አዎን ስሜ ነው አለች፤ ጌታው አልዩም ባሉዋ ይኸው ነው ስሙዋ አለ፤ ያንጊዜም ፊታውራሪ በላይ ያ አቶ በላይ ይባል የነበረው ያባይ ውሃ ሙላት ሲወስደው ሚስቱ እያለቀሰችና እየተከታተለች ላይኑዋ እስኪጠፋ ድረስ የተመለከተችው ሰው የዛሬው ፊታውራሪ በላይ እዚህ እመኻላቸው ቆሜ ያለሁት እኔው ራሴ ነኝ ብሎ ሲናገር ታላቅ አሳብ የሚያንቀሳቅስ

የሚያስደንቅ ስሜት ነገሩን በሰማው ባደባባዩ ሰው ሁሉ ላይ የሰጠ ኖኖ ሁለት ደቂቃ ያህል ዝምታ ሆነ። ከሱም ግራና ቀኝ የቆሙት ከሳሾችና ተከሳሾች ደንግጠው ዘወር ብለው እሱን እያዩ ይመለከቱት ጀመር።

ወዲያውኑም ፊታውራሪ በላይ ያን ጊዜ ውሃው ሲወስደው የዛፉ ግንድ አግኝቶ በዚያ ተደግፎ እየሄደ ጥቂት ፋታ ማግኘቱን ይኸንኑም ግንድ እየተደገፈ ብዙውን መንገድ በውሃው ላይ ከሄደ በኋላ ወንዙ ከሚታጠፍበት አንድ ገመገም ቦታ ላይ ዛፉ ተደስሞና ተጋግቶ መሬት ወግቶ እንደ ቀረ በዚያውም በኩል የየብሱ መሬት ጠረፍ ላይ የበቀለ ትልቅ ዛፍ ክንፉ ወደ ወንዙ የተዘረጋ ስለ ነበረ በብዙ ችግር እዚያ ተጠግቶ ቅርንጫፉን ይዞ መውጥት እንደ ቻለ ከዚያም በኋላ ራቁቱን ስለ ነበረ ቅጠል መሳይ ቈራርጦ አስሮ ለብሶ መንገድ እየፈለገ ሰው ወደሚገኝበት ለመድረስ ሲሄድ ጊዜው መሸቶበት ከሩቅ እሳት አይቶ በብዙ ችግር ከሌሊቱ ወደ ስድስት ሰዓት ሲሆን ከዚያ መድረሱን ከደረሰም ወዲያ የሰፈሩ የነጋዴው ጕረደማኖች ሌባ ነው ብለው አስረው መደብደባቸውን ዋናውም ጌታቸው ነጋዴው መጥቶ ነግሩን ጠይቆ እንዳይመቱት ከልክሎለት እስራቱን አስፈትቶ ባልደረባም ሰጥቶት ልብስ እንዲያገኝም አድርጎ በደኅና ማሳደሩን በማግሥቱ ጥዋት ግን ብርዱ በሰውነቱ የጠለቀው ውሃው ያጕላላውና ጕረደማኖች የደበደቡት አካላቱ ሁሉ አብጦ በጠና መታመሙን፤ ነጋዴውም በጣም አዝኖለት በክብት አስቀምጦ የሚደግፉትም ሰዎች አድርጎለት ይዞት ተጕዞ ከግንደ በረት ከተማ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ዘንድ እንዲያስታምሙለት ገንዘብ ጭምሮ ሰጥቶ ትቶት መሄዱን ከሦስት ወር በኋላም በነ ስለ ሆነ ዐባይ አፋፍ ጎሐ ጽዮን ድረስ ሄዶ የሚስቱንና የልጆቹን ወሬ ለማግኘት መንገደኞች እየጠየቀ ጥቂት ቀን መሰንበቱን፤ ከጠየቃቸውም መንገደኞች ስለ ቤተ ሰዎቹ ምንም የሚያመለክት ወሬ አለማግኘቱን ከዚያም በኋላ ተስፋ ቈርጦ ወደ ሸዋ ከተማ እንጦጦ መምጣቱን፤ እንጦጦም እንደ ደረሰ ጥቂት ሰሞን ያንን ውለታ የዋለለትን ነጋዴ ስሙን አያውቅም ነበርና በመልኩ እየፈለገ በየነጋዴው ሰፈርና በየገበያው መቈየቱን፤ ነጋዴውንም ሳያገኘው ለትዳሩ ኑሮ ጌታ ፍለጋ ወደ ሐረርጌ መሄዱን ያንንም ይፈልገው የነበረውን ነጋዴ

ከዐሥራ ሁለት ዓመት በኋላ እዚያው ድንገት አግኝቶት ጊዜው በመቈየቱ መልኩ ተሳስቶት በጥያቄ ብዛት እሱ መሆኑን አረጋግጦ ማወቁን ይህንኑም ነጋዴ ከራስ መኰንን ጋራ አገናኝቶት ነጋዴው እዚያው የራስ መኰንን አሽከር ሆኖ መቅረቱን፤ በኋላም የሐረርጌን ነጋድራስነት ተሾሞ ያን ጊዜም ለዘመቻው ሥንቅና መሣሪያ አስጭኖ መጥቶ ነበርና አብሮ እዚያውም አደባባይ ተቀምጦ ስለ ነበረ፤ እሱንም አመልክቶ አሳይቶ ካደጋው ቀን ጀምሮ የደረሰበትን ሁሉ እንደ ተቻለው በማሳጠር ዋና ዋናውን ነገር ተናግሮ አስታወቀ።

ያን ጊዜም ያም ነጋዴ እዚያው አደባባይ ተቀምጦ በመገኘቱ ሁሉንም ነገር ይሰማ ነበርና ወዲያውም ተነሥቶ ነጋድራስ ገብረ መድኅን ይኸውም ነገር ከሆነ ፳፩ ዓመት መሆኑን፤ እሱም ራሱ የሚያውቀውን በዚያን ጊዜ የደረሰበትን ሁሉ ስለ እርሱ አመልክቶ ተናገረ።

ዳኞቹና ተቀማጩም በጉባኤውም የነበረው ሰው ሁሉ የሆነው በሕይወታቸው ኑሮ ላይ ያለፈውን ታላቅ ታሪክ ያለውን መከራ ሁሉ ከሰሙት በኋላ በመገረም የተናወጠው አሳባቸው ጥቂት በጥቂት ቶሎ መረጋጋት ጀምሮ በዚያን ጊዜም ዋናው ዳኛ ወዲያው ተነሥቶ ጌታው አልዩን የቦሩ ሜዳውን ጭቃ ሹም ሁሉንም ነገር አሁን የሰማኸው ነው ምንድነው እንግዲህ ስለዚሁ ስለ ተከሰስክበት ጉዳይ የምታስታውቀን ብሎ ጠየቀው፤ በሚፈርደው ነገር ጥቂት ስለተቸገረ፤ በዚያን ጊዜም ባለጉዳዮቹ ሰውነታቸውን የቃኘውና ያናወጠው መንፈስ ተንቀሳቅሶ በቅኔ ያናግራቸው ጀመረ።

> እ - እ - አሁንማ ብሎ ጌታው አልዩ፤
> ከባሶ ከሶዶ ልጅችዋን ጐትቶ
> ባልዋን ካባይ ሙላት በታሪክ አውጥቶ
> በሐረር አዙሮ ደግሞ እዚህ አምጥቶ
> እሱዋንም እኔ ዘንድ ለጉድ አቈይቶ
> ሲያጋጥም ሰብስቦ ሁሉን አገናኝቶ
> ምን እምለው አለኝ ነገሬ ተረትቶ።

ወይዘሮ ተዋበች።
ሰው ለምን ይሆን ትንሳኤ እማያምነው
ሞቶ የተነሣን እንዲህ እያየነው።
አሸነፍሁት ያለኝ ውሸቱን ነው ዐባይ
ይኸው አየዋለሁ ጥልቶ መጥቷል በላይ።
እልል በሉ ሰዎች ፍሪዳም ደግሱ
መጥተዋል እንግዶች ከሞት የተነሡ።
ልጆች ካሣሁንና ጌታነህ።
የንጋትዋ ኮከብ ከግቢዋ ወጥታ
እሸብሩ ቦታ እኛ መኻል ገብታ።
በለስላሳው ቃሉዋ ራሱን መታችው
ያለ ጦር መሣሪያ ጠቡን ገደለችው።
የመጣችው እናት ቀድማ ለማገልገል
ለማዳን ሆነ ወይ እኛን ከመጋደል።
ያባይ ውሃ ሙላት ሲያወጣ ሲያወርደው
አባትን እንዲያድን አፉን ማን ሰደደው
ምንድነው ይኸ ቀን ያፈለቀው ነገር
ባባትና በናት ልጆችን ለማክበር።
ፊታውራሪ በላይ።
መንፈሱ እየቃኘን አናወጠን ኃይሉ
ታላቅ ስሜት ሰጠ ለሰውነት ቃሉ።
ተድላና መከራ አብረው ይዞራሉ
ደካማና ብርቱን ሰው ይፈትናሉ።
በመከራም ይልቅ አድካሚ ነው ተድላ
ሲሻ ከንቱ ነገር መንፈስ እያላላ።
በፍቅሩ የሚኖር ቢበዛ ሕመሙም
አይወድቅም በዋዛ ይድናል ከሁሉም።
ያየነው ዛሬ ቀን ድንቅ ነው ባይናችን

ያምላካችን ፍቅር ይንገሥ በላያችን።
ብዞች የማያዩት ትልቅ ነው ጥበቡ
ለማዳን ሲፈቅድ ይገኛል ሰበቡ።
እንበርታ እንዋጋ ፍቅርን ለመሻት
ይቅር የሚያሠጋን ንፍገትና ኵራት።

ነጋድራስ ገብረ መድኅን።

ከንግዴ ዕቃ ሁሉ እስካሁን ካኖረኝ
መልካምነት ብቻ እጅግ አስከበረኝ።
በጣም የበዛ ነው ዋጋው መልካምነት
የለም የሚመስለው ይታመናል በውነት።

ዋናው ዳኘ።

እውነት እንናገር አሁንስ አንፍራ
እነሆ እናያለን የኣተምር ሥራ።
ያንዳንድ ጥፋተኛ ነገር በመመርመር
እጅግ እንደከማለን በጣም በመቸገር።
አንዳንዱም ጃውሳ የሚያመልጥ አይጠፋ
ነገሩን የሚገልጥ መስካሪ እየጠፋ።
ባባይ ምስክርም ደኅና ሰው ይሞታል
ምንም መልካም ቢሆን ዳኛም ይሳሳታል።
ብዙ ችግር አለ በሰው ፍጥረት ኑሮ
የውነት ነገር ሲቀር ሐሰቱ ተከብሮ።
ስለዚህ በስውር እየብዛ ጥፋቱ
ደኅናው ሰው ይላላል ለእውነት ከመገዛት።
እውነትህ ዘወትር እንዲሁ ቢገለጥ
ክብርህ ይሆን ነበር እያደር የሚበልጥ።

****



## ስለደራሲው በጥቂቱ

በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት በጉርሱም አውራጃ ኅዳር 1885 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ በተወለዱ በወራት ጊዜ ውስጥ እናታቸው ሞቱ፡፡ ዕድሜያቸው አራት ዓመት ሲሆናቸው ወላጆቻቸው ከሞቱባቸው ሌሎች ልጆች ከሚያድጉበት ከራስ መኮንን ቤት እየተማሩ እንዲያድጉ ተላኩ፡፡ እዚያም በአብዛኛው ግዕዝና ሌሎች ትምህርቶች ተማሩ።

እምሩ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በጣም ይታወቃሉ፡፡ ከምኒልክ ጊዜ ጀምሮ እስከ ደርግ ሥርዓት ድረስ መኖራቸው ደግሞ በበለጠ ለመታወቅ አስችሏቸዋል፡፡ ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ ከሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸው ስለኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ ዲፕሎማሲና ወታደራዊ ታሪክ አጉልተው ጽፈዋል፡፡

ምንጭ: የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

### የደራሲው ሥራዎች

1. ዓለማዊ ትግል (**ግጥምና ቅኔ**)
2. ፊታውራሪ በላይ (**ተውኔት**)
3. ሰውና እውቀት (**ተውኔት**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY